# ቀበና

## አብሮ አደጎች



## የ25ኛ ዓመት ዝክረ በዓል ልዩ መጽሔት

ይህ ልዩ መፅሔት በሞት ላጣናቸው ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን መታሰቢያ ይሁን!

Design + Print By:
Queen of Sheba Printing & Adv.
0911423584/ 0118-101255

ሚያዚያ 2009 ዓ.ም

# Life Addis Clinic

## ✓ Gives Services on

- General Medicine (internal Medication)
- Pediatrics Service
- Surgery (Minor operation)
- Circumcision

የአካባቢው ነዋሪ
ልዩ
ባለውለታ!

## ✓ Ultrasound

## ✓ Family planning program

- MCH
- ANC follow up

## ✓ General Laboratory

## ✓Services

- CBC (Hematology)
- Chemistry
- Serology
- Parasitology
- Urine analysis
- AFB, Gram Stain
- Wet Smear
- Blood Film


## ✓ General Laboratory

## ✓Services


"Life is Life, fight for it"
"Life is a promis. Full-fill it"
Mother Theresa
(We share the above quotes)


Address:- 4 Killo near Ginfile Bridge Arada Sub city Woreda 7
(Keftegna 13 Kebele 08) Tel +251-118-10 57 47

# የመፅሔቱ አዘጋጆች ቡድን



**ዋና አዘጋጅ**

- ታዬ አየለ

**ምክትል አዘጋጆች**

- ግርማ ገመቹ
- ገዛኸኝ ጽዋመስቀል

**የኤዲቶሪያል ኮሚቴ አባላት**

- ዶ/ር ብርሃኑ ተክሌ
- ምንዳ ተሰማ


# ማውጫ


- የሊቀመንበሩ መልዕክት 1
- ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ የቀበና ኮርያ ሠፈር ታሪካዊ አመሰራረት 2
- የቀበና ኮርያ ሠፈር ባለርስቶች አመጣጥ በቻርት ሲገለጽ 4
- ያጋጣሚ ነገር 5
- መቼም ለአፍታ እንኳን አትረሱም 6
- ዘመን ተሻጋሪ ነዋሪዎቻችን 7
  - አባባ ሳላ ደቻሳ
  - ጋሼ አረሩ ገድሌ
  - ቴምባና ደጼና
- ጋሼ ታምሩ ዮሴፍ 8
- ሐኪሜዳና ትዝታዎቼ 10
- ሐይሌ ዱቤና ዱቤ ባሕር 15
- የቀበና ስፖርት ትውስታዎች 17
- የጨዎታ ቦታዎቻችን ትዝታዎች 18
- ከፎቶ ማሕደራችን ድሮ 19
- ከፎቶ ማሕደራችን ዘንድሮ 23-26



## ምስጋናችን ይድረሳችሁ

1. ዶ/ር መሳፍንት አበበ ለመጽሔቱ የሕትመት ወጪ ከፍተኛ የገንዘብ እርዳታ ያደረጉልን በመሆኑ !
2. አቶ መአዛ ስመኝ ስለ ቀበና አመሰራረት ዋቢ የሚሆን መረጃ ስላካፈሉን !
3. ኮሎኔል አሰፋ ወ/የስ ስለ ቀበና አመሰራረት ዋቢ የሚሆን መረጃ ስላካፈሉን !
4. ገዛኸኝ ፅዋመስቀል በቀበና እና ዙሪያ የነበረውን የስፖርት እንቅስቃሴ ስለዘገቡልን !




# የሊቀመንበሩ መልእክት

የተከበራችሁ የዚህች መፅሔት አንባቢያን በሙሉ በቅድሚያ እንኳን ለ25ኛው የቀበና ኡብሮ አደጐች ዝክረ በዓል አደረሳችሁ የ25 ዓመታት ጉዞ ስናስብ የማሕበሩ አመሰራረት ምን ይመስል እንደነበር ማውሳት ተገቢ ይመስለናል። ማሕበሩን ለማቋቋም እርሾ ሆነው የጀመሩት ስምንት አባላት ሲሆኑ በመጀመሪያው ስብሰባም መስከረም 27 ቀን 1983 ዓ.ም በአቶ የወንደሰን ተፈራ መኖሪያ ቤት ከምሽቱ 12፡30 ላይ የነበረ መሆኑን በወቅቱ ተይዞ የነበረው ቃለ ጉባኤ ይመሰክራል ይህ እለት በሁላችንም ህሊና ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው።

ማህበራችን ከተመሠረተበት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በረጅም ጊዜ ሊተገበር የሚችል ማህበራዊ አገልግሎቶችን መስጠትና ከዚህም ጋር በተያያዘ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ተቋማትን በመመስረት ለሠፈሩ ኗሪዎች ጠቃሚ አገልግሎቶችን ማበርከት የሚል ነው።

ይህን ዓላማ እስከ ዛሬ ለማሳካት የተለያዩ ችግሮች ቢገጥሙትም ወቅታዊና አጋጣሚዎች በሚፈጥሩት ክስተቶች ለኗሪዎቻችን አቅም በፈቀደ መጠን ድጋፎችን አድርገናል። ለአብነት ለመጥቀስም በክብር ዘበኛ ካምፕ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የቀድሞ ሠራዊት አባላት ተፈናቅለው በዱቤ ባህር አካባቢ በመጠለያ ሥፍርው በመኖር ላይ እያሉ በአጋጠማቸው ድንገተኛ የእሳት ቃጠሎ ንብረታቸው ለወደመባቸው ከፍተኛ የገንዘብ እርዳታ አድርጓል።

የቀበሌው አስተዳደር ለወጣቶች ቤተ መጽሐፍት ቤት ለማቋቋም በአቀደበት ጊዜም በግንባር ቀደምትነት ቁጥራቸው 25 የሚደርሱ አጋዥ የትምህርት መጻህፍትን ገዝቶ አስረክቧል። ይሁንና ተቋቋመ የተባለው ቤተመጻህፍት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሲፈርስ መጽሐፍቶቹ ዛሬም የት እንደደረሱ የሚናገር ሰው አልተገኘም። በተጨማሪም በአካባቢያችን ካሉት ዕድሮች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙና የእድር ወርሃዊ ክፍያ መክፈል ለማይችሉ እናቶችና አባቶች አንድ ዓመት ክፍያ ለመሸፈን ሶስት እድሮችን በደብዳቤ ጠይቅን መርጠው ለላኩልን አሥራ ሰባት ደካሞች የአንድ አንድ ዓመት ድራሻቸውን ወርሃዊ ክፍያ ሸፍነናል።

ለወደፊቱም ለተጠናከረ ዕቅድ የገንዘብ አቅማችንን በማሳደግ ከበፊቱ ላቅ ያለ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት እየተዘጋጀን ነን።እግዚአብሔር ከጎናችን ይሁን አሜን።

ይህ ማሕበር በኮርያ ሰፈር አካባቢ ልዩ ስምና እውቅና ያለው ሲሆን ይህም ባለፉት አመታት በሞት ያጣናቸው ወንድሞቻችንና እህቶቻች ብርቱ ጥረት መሆኑ አያጠያይቅም። በመሆኑም የዚህች መፅሔት ዓላማ የዚያን ዘመን ቀበና (ኮ/ሠፈር) ታሪክ ለመጪው ትውልድ ከማስተላለፍ ባለፈ ለእኒያ በሞት ላጣናቸው ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ማስታወሻ እንዲሆን ለማድረግ ነው።

ይህ ማሕበር የተለያየ ይዘት ያላቸውን መጽሔቶችን በማሳተምና በማሰራጨት ከህብረተሰቡ ጋር እራሱን ያስተዋወቀና ያላመደ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደጋጋሚ በወንድሞቻችንና እህቶቻችን ላይ በደረሰው የሞት አደጋ ምክንያት ስሜታችን በመቀዛቀዙ ይህ ተስተጓጉሎ ቆይቷል።

ይህች መጽሄት የቀበናንና አካባቢውን አመሰራረት፣ ጉምቱና አንጋፋ ነዋሪዎቿን፣ የዘመኑ ታዳጊዎቹን እና ሌሎች ቁምነገሮችን አካታ የሆድ የሆዷን ልታጫውተን እነሆ ለአንባቢያን ቀርባለች በጥሞና እንድታነቧት አበክሬ በአክብሮት እጋብዛለሁ።

በመጨረሻም ይህን ታሪካዊ 25ኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ ዓመታዊ አከባበር ወቅት የማሕበሩ ሊቀመንበር ሆኜ በመገኘቴ እና ይህን መልዕክት ለማስተላለፍ በመቻሌ የተሰማኝን ደስታ በዚህ አጋጣሚ እገልፃለሁ።

እግዚአብሔር የቀበና ኡብሮ አደጐች ማሕበርን ይባርክ!

አመሰግናለሁ መልካም ንባብ

ግርማ ካሳሁን የማሕበሩ ሊቀመንበር

# 1. ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ

## የቀበና ኮሪያ ሰፈር ታሪካዊ አመሰራረት

ነገርን ከሥሩ ውሃን ከጥሩ እንዲሚባለው ሁሉ ቀበና የወንዝ ስም ነው። ከሰሜን እንጦጦ ጋራ ሥር ተነስቶ ወደ ደቡብ በረጅሙ ተጉዞ አባ ሳሙኤል ሐይቅ የሚገባው ይህ ወንዝ ስያሜው ሲነገር እንደሚሰማው ከአዲስ አበባ ከተማ ምስራቃዊ ቆላ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ከብት አርቢዎች ለግጦሽ ወደ ደጋው ሰሜናዊ አቅጣጫ ይንቀሳቀሱ ነበር ይባላል። በዚህ ጉዞ ከብቶቻቸውም ሆነ እራሳቸው ውሃ የሚጠጡት ከዚሁ ወንዝ ነበር። አንድ ቀን ታዲያ አንዱ በከፍተኛ ሁኔታ ተጠምቶ የነበረ ባላገር ከወንዙ የጥማቱን ያህል ከጠጣና እርካታ ካገኘ በኋላ በአፍ መፍቻ ቋንቋው "ቀበና" የሚል ቃል ተናገረ። ሲተረጎም ቀዝቃዛና የሚያረካ ማለት እንደሆነ አንጋፋዎች ይነግሩናል። በዚሁ ወንዙ ቀበና ተብሎ መጠሪያው ሆኖ ቀረ ።

**ሰፈሩስ እንዴት ተመሰረተ?** ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ምላሽ ማግኘት የተቻለው ዕድሜያቸው በሰባዎቹ እና በሰማኒያዎቹ ውስጥ ከሚገኙ የሠፈሩ አንጋፋ ተወላጆች ነው፡፡ ለቀበና ሰፈር መመስረት ዐቢይ ሚና የተጫወተው የዳግማዊ ምንሊክ ሆስፒታል መቋቋም ነው።

ዐፄ ምንሊክ ሆስፒታሉን በ1902 ዓ.ም ሲያቋቁሙ ከቤተመንግስት ባለሟሎች መካከል ለአቶ ሣላ ደቻሣ ፣ ለአቶ ቦና (የአባታቸው ስም ያልተገኘ) እንዲሁም ለወ/ሮ አስካለ ኦዳ (የአቶ በቀለ ካሣ እናት) በሆስፒታሉ ሰሜናዊ ምስራቅ አዋሳኝ ላይ ዳግማዊ ሚኒሊክ ርስት ሰጥተዋቸው መኖሪያ ቤታቸውን በሳር ጎጆ ሰርተው እኒሁ ሰዎች መኖር ጀመሩ። የአቶ ሣላህ መኖሪያ ቤት ዛሬም አለ።የአቶ ቦና ርስት ለልእልት ወለተ እሥራኤል ተሸጦ ትልቅ ዘመናዊ ቪላ ቤት ተሠርቶበት ዶክተር ባቡር ይባል የነበረ ጀርመናዊ የቀዶ ጥገና ሀኪም ይኖርበት• የነበረ ነው። ቤቱ ቢጎሳቆልም ዛሬም አለ።የወ/ሮ አስካለ ኦዳ ቦታን ልጃቸው አቶ በቀለ ካሣ ወርሰው መኖሪያ ቤቶች ሠርተውበት የልጅ ልጆቻቸው ዛሬም ይኖሩበታል።

እንግዲህ የእኛዋ ቀበና ላይ የመጀመሪያዎቹ ሠፋሪዎችና መኖሪያ ቤቶች የተገነቡት በእነዚህ የምንሊክ ባለሟሎች ነበር። ከዚያ በኋላ ነው ሌሎች የመሬት ባለርስቶች በአካባቢው የሠፈሩት እነዚህም ከወ/ሮ አስካለች ኦዳ ርስት ሰሜናዊ አቅጣጫን ይዞ ነጋድራስ ጳውሎስ፣ ከአቶ ሳላ ደቻሣ ጎን እስከ ሬሣ ቤቱ መዳረሻ፣ ደጃዝማች ገድሌ ወ/መድህን፣ የክብር ዘበኛ ግዙፍ የግንብ አጥር ፊት ለፊትን ይዞ እስከ ቀበና ወንዝ ድረስ ሊቀመኳስ አጥናፍ ሰገድ ባለ ርስተ ጉልት ሆኑ። (መግለጫውን በገጽ 3 ይመልከቱ) እነዚህ ሦስቱ ባለ ርስቶች የአንድ አያት ልጆች ነበሩ ይባላል። ደጃች ገድሌና ሊቀ መኳስ አጥናፍ ሰገድ ከታላቁና ገናናው የአድዋ ጦርነት ድል መልስ አዲስ አበባ ሲገቡ የገበሬ ጦራቸውን እንዲያሰፍሩበት መሬት ይሰጣቸዋል ይሁንና የገበሬው ጦር ወደ የመጣበት ትውልድ ቦታው በመሄድ ሲበተን ቦታውን በግል ርስትነት እንደያዙት ይነገራል። ነጋድራስ ጳውሎስ የእነ ልጅ አርጋው ጳውሎስ አባት ማለት ናቸው ዘመናዊ ትምህርት በውጭ ሀገር እንደቀሰሙና በርስትነት የያዙት ቦታ የሲራራ ነጋዴዎች ከአጋሰሶችና ከግመሎቻቸው ላይ የንግድ ቁሳቁሶቻቸውን የሚያራግፉበትና የሚጭኑበት አካባቢ ስለነበር እርሳቸው ነጋዴዎችን ቀረጥ እንዲቀርጡ በቦታው ምንሊክ ይሾማቸዋል። በዚህ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ አካባቢውን በርስትነት እንደያዙት ይነገራል።

ከቀበና ኮርያ ሰፈር ቀደምት ኗሪዎች መካከል ነጋድራስ ጳውሎስ ያሲን አንዱ ናቸው። እኚህ ታላቅ ሰው በወሎ ጠ/ግዛት ልዩ ስሙ ጃማ ተብሎ በሚጠራው አከባቢ ተወላጅ የነበሩና በዐፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት ባህር ማዶ ተሻግረው በፈረንሳይ ሀገር ዘመናዊ ትምህርት ይከታተሉ እንደ ነበር ታሪክ ይነግረናል። (ፎቶውን ይመልከቱ)

የሥልጣኔ አባት የነበሩት ዐፄ ምኒሊክ ኢትዮጵያን ከአውሮፓ ሀገራት እኩል የተራመደችና የሰለጠነች ሀገር እንድትሆን በነበራቸው ታላቅ ራዕይ በውጭ ሀገር ይማሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያንን ወደ ሀገራቸው ገብተው የአስተዳደር ሥራዎችን እንዲሰሩላቸው ጥሪ ሲያቀርቡ ከነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝና ከሌሎች ምሁራን ጋር ጳውሎስ ያሲን ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ምንሊክም ወጣቱ ጳውሎስ የተማረውን ጠይቀው በተረዱት መሰረት የአሁኑን ጉምሩክ መ/ቤት ጥንስስ የነበረውን የቀረጥ ሰብሳቢ ሹም አድርገዋቸው ማዕረጉንም ነጋድራስ የሚል ሹመት ሾሟቸው ትርጉሙም የነጋዴ ራስ ወይም የነጋዴዎች የበላይ እንደ ማለት ነበር።

ጳውሎስ ያሲን ይህን ኃላፊነት ይዘው በግላቸውም የንግድ ሥራን እየሰሩ ቀረጥ ይሰበስቡ ጀመር። አሁን ተወላጆቻቸውም የአሉበት ሥፍራ የሲራራ ነጋዴዎች ግመልና በቅሎ እንዲሁም ሌሎች የጭነት እንስሳት የሚያርፉበትና የሚተላለፍበት ነበር። በዚህ አካባቢውን ነጋድራስ ጳውሎስ በርስትነት ይዘውት ለልጆቻቸው አስተላልፈዋል። በዚህ ስሌት ስንሄድ ከአድዋ ጦርነት በፊት በቀበና የሰፈሩት ነጋድራስ ጳውሎስ መሆናቸው ታምኗል። ቀሪዎቹ ባለርስቶች እነ ሊቀመኳስ አጥናፍ ሰገድ፣ ደጃዝማች ገድሌ እና ሌሎችም ከአድዋ ጦርነት መልስ ሠፈሩን የመሰረቱ ነበር ማለት ይቻላል።

እነዚህ የዘመነ ምንሊክ ሁለተኛ ባለርስቶች ለልጆቻቸው መሬት አደላድለው ሲያልፉ ልጆቻቸው ለቤት ሰሪዎች በዚያ ዘመን ቋንቋ መሬትን በጭሰኝነት መምራት ጀመሩ፤ አመራሩም በግምት ከዚህ እና ከዚህ መለስ በሚል በካሬ ሜትር ከ 0.10 ሳንቲም - 0.20 ሳንቲም እንደነበር በህይወት የአሉ አዛውንት ኗሪዎች በትውስታ ተመስጠው ያወጉታል።

ቀደምት የጭሰኝነት ተመሪዎች ውል ይገቡ የነበሩት የሣር ጎጆ ቤት ሊሠሩ፣ ባለ ርስቱ ተነስ በሚልበት ወቅት ጎጆውን አፍርሰው ካሳ ሳይጠይቁ ሊነቀሉ ግዳጅ ገብተው ነበር። በዚህ ሁኔታ ከእነ አቶ ሣላ ደቻሳና ጓደኞቻቸው በተጨማሪ አልፎ አልፎ የቆርቆሮ ቤቶችና በአጠገቦቻቸው የተራራቁ የሣር ጎጆ ቤቶች ተሠርተው የኗሪዎች ቁጥር መጨመር ጀመረ።




ከቀበና መስራች አባት አንዱ የሆኑት ነጋድራስ ጳውሎስ ያሲን ከመቶ ዓመት በፊት

ምንጭ፡- አቶ ግዛው ደበበ


በቀበና ፈጣን የኗሪዎችና የቤቶች ቁጥር መበራከት የጀመረው ከ1943-1947 ዓ.ም ባሉት አራት ዓመታት ውስጥ መሆኑ ዕድሜ ጠገብ ኗዋሪዎች ይመሰክራሉ። የቀድሞዋ “ቀበና” ኮሪያ ሰፈር ወደ ሚለው ስያሜ የተሸጋገረችው በዚሁ ወቅት ነበር።

የክቡር ዘበኛ ወታደሮች ቃኘው የሚል ስም ይዘው ኮሪያ በተባበሩት መንግስታት የሰላም ማስከበር ግዳጅ ተሰማርተው አኩሪ ገድል ፈጽመው ሲመለሱ በተሰጣቸው ገንዘብ መጠለያ ለመስራት ዓይናቸው ያረፈው ቀበና ላይ ነበር። ይህም በሁለት ምክንያት ነበር አንድ የክብር ዘበኛ ጦር ካምፕ ለቀበና ቅርብ በመሆኑ ሲሆን ሌላው በዚያ ዘመን የውሃ ቧንቧ ስለአልነበረ ለመጠጥም ሆነ ለንጽህና ውሃ በቅርብ ለማግኘት ቀበናን እንደመረጡት አንድ አዛውንት አጫውታውናል። እናም እንደ ቅርበታቸውና ባህሪያቸው ተቧድነው ጭሰኞች የቀበና ባለርስቶችን ደጃፍ አንኳኩ ተከፈተላቸው ያሰቡትንም የቦታ ምሪት አገኙ። ታዲያ እነሱ የዘመን ለውጥ ረድቷቸው የሳርቤት ጎጆ ግዳጅ አልተጣለባቸውም። ቤቶቻቸውን በቆርቆሮ መሥራት ቻሉ የቦታው ምሪት ዋጋ ከበፊቱ አልጨመረም ያው ነበር ይባላል። ወታደሩም ክ.ዘ. በየአቅጣጫው ቤቱን በቆርቆሮ ገጠገጠው ቀበናም ኮሪያ ሰፈር የሚለው ስሟ በክብር ዘበኞች ሰፈር ፀደቀላት።

የእኛዋ ቀበና ኮሪያ ሰፈር የጥንቱም ሆነ የዛሬ ወሰን በሰሜን ገድሌ ምንጭን ይዞ ቁልቁል ቀበና ወንዝ ይገባና የወንዙን ዳርቻ እየተከተለ ወደ ደቡባዊ ምሥራቅ ተጉዞ ዱቤ ባህርን ተሻግሮ ጀርመን ድልድይ ሳይደርስ ሽቅብ በሀኪም ሜዳ የዳግማዊ ምንሊክ ሆስፒታል የግንብ አጥር ተከትሎ ሬሣ መውጫ ይደርሳል። የክብር ዘበኛ ግንብን ይዞ ገድሌ ምንጭ ድረስ ያለውን ቦታ አካሎ ያበቃል። ቀበና ዳግማዊ ምንሊክ ሆስፒታል ተመስርቶ ከተመረቀበት 1902 ዓ.ም ጀምሮ ሲቆጠር እስከ ዛሬ የ106 ዓመታት የዕድሜ ባለፀጋ ናት።

የቀበና አመሰራረት በአጭሩ ይህን ይመስላል። ለሁሉም መልካሙን ሁሉ ለቀበና እንመኛለን።

# 2. የቀበና ኮሪያ ሰፈር የቀድሞ ባለርስቶች አመጣጥ በተዋረድ ሲገለጽ




<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ይህን መረጃ የሰጡን ሰዎች በዕድሜ የገፉ በመሆናቸው በአእምሮአቸው የመጡላቸውን ተወላጆች ገልፀውልናል ምናልባት ያልተካተቱ ተወላጆች ካሉ የመፅሔቱ አዘጋጆች ይቅርታ ይጠይቃሉ።

<u>ምንጭ፡-</u>

1. ወ/ሮ ማሚቴ እንዳሻው የልጅ አለማየሁ አጥናፍሰገድ ባለቤት በቅርቡ በሞት የተለዩ
2. ወ/ሮ ዘውድነሽ ወየሣ
3. አቶ ከበደ ሣላ በኮርያ ሠፈር ተወልደው ያደጉና የኖሩ መረጃ ከሰጡ በኋላ በሞት የተለዩ
4. አቶ መሀዛ ስመኝ

# 3. የአጋጣሚ ነገር (ስምን መልአክ ያወጣዋል)

ያለፈ ድርጊት ክስተት ሁሉ ያለፈ ነውና ታሪክ ይሆናል። አጋጣሚው በፈቀደለት ቦታና ጊዜ ይወራል፤ ይደመጣል፤ ያስደምማል፤ የኖረውና የነበረው ሲከስም ታሪክ ሆኖ ያልፋል፣ ነገሩ እንዲህ ነው ይህችን መጽሔት ለማዘጋጀት በተደረገው እንቅስቃሴ ለቃለ መጠይቅ ከጋበዝናቸው ነባር ኗሪዎች መካከል አንዱ ኮስተር ብለው " ለመሆኑ ይህ የማህበራችሁን ስያሜ ከምን ተነስታችሁ ሰጣችሁት?" አሉን። እኛም ቀላል ጥያቄ አድርገን በመውሰድ ተወልደን አብረን ያደግን ስለሆነ ስያሜው ከዚያ ነው አልናቸው። ቀጠሉና "ከእናንተ በፊት ከ 50 ዓመታት በፊት በዚሁ ስያሜ ማህበር እንደነበር ታውቃላችሁ?" አሉን።

ተገረምን ታሪኩን ለማወቅም ጉጉት አደረብንና ኧረ አናውቅም የሚል ፈጣን ምላሽ ሰጠናቸው። ዘና ብለው ፈገግ አሉ። በዝምታ ፈረስ ወደኋላ ነጎዱ አሰቡ አሰላሰሉና ጉሮሮአቸውን ጠራርገው አዳምጡኝ ከአባላቶቹ ዝርዝሩን ላስረዳችሁ አሉን። ጀመሩ "የቀበና አብሮ አደጎች ማህበር በ 1957 ዓ.ም ተቋቁሞ በርካታ ማህበራዊ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየነበር።" አሉን አሁንም ለጥቂት ሰኮንዶች በዝምታ ሰማይ ሰማይ አይተው መለስ ብለው የአባላቶቹን ስም ከነስራ ድርሻቸው ዘረዘሩልን።

1. **ኮሎኔል ወርቁ ዳዲ - ሊቀመንበር**
2. **አቶ መዓዛ ስመኝ**
3. **አቶ ተስፋዬ አርጋው**
4. **አቶ ክፍሌ ማርቆስ**
5. **አቶ አበበ ተፈራ**
6. **ወ/ሮ አስካለ ቸርነት**
7. **ወ/ሮ አስቴር ሀይሌ**
8. **አቶ እሸቱ ምንዋብ**
9. **አቶ ከበደ ሣህሌ - ፀሐፊ**
10. **አቶ ደምሴ ሰይፉ - ገንዘብያዥ**
11. **አቶ ልሣኑ በቀለ**
12. **አቶ ዘውዴ ተፋረደኝ**
13. **አቶ ጥላሁን ወ/ማርያም**
14. **አቶ ጋሻው ገ/ማርያም**
15. **አቶ በቀለ አየለ**
16. **አቶ ሀይሉ ስሙንጉስ**
17. **አቶ ጥበቡ ከተማ**
18. **አቶ ጥበቡ ደስታ**
19. **ወ/ሮ ማሚቱ ተበጀ**
20. **ወ/ሮ ቆንጂት አርጋው**
21. **ወ/ሮ አለሚቱ**
22. **አቶ ተስፋዬ በላይነህ**

አዳምጠን መዝግበን ስንጨርስ አሁን አሉ? እሺ አልናቸው። የቁጭት ሳቅ ሳቁና ኮስተር ባለ ድምፀት በ1968 ዓ.ም በጊዜው የፖለቲካ ወጀብ ምክንያት ሊቀመንበሩ ላይ ስጋት ተፈጥሮበት ማህበሩ እንዲፈርስ ተደረገ አሉን። እኛም በታሪኩ አዘንን ግን የማህበሩ ስም ሞቶ አልሞተም ስምን መለአክ ያወጣል እንዲሉ ተከታዩ ትውልድ ስሙን ይዞ ይኸው ቀጠለ።

## 4 . መቼም ለአፍታ እንኳን አትረሱም

አብረን ያሳለፍናቸው የመተሳሰብ፣ የመረዳዳት፣ የደስታና የፍቅር ጊዜያቶች ምን ጊዜም ከፊታችን የሚጠፋበት አጋጣሚ የለም። ወደፊትም አይኖርም። የቁም ነገር ወጎቻችን የእርስ በርስ ቅርርባችን የሳቅ ጨዋታ ጊዜዎቻችን ከቶም አይረሳም። ዞሮ ዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት የሚለው ብሂል ለእናንተ ሞት መጽናኛ ሊሆነን አይችልም።የእኛ መጽናኛ የሚሆነው መቼም ለአፍታ አንኳን የማንረሳችሁ መሆኑ ነው። አዎ መቼም ለአፍታ እንኳን አትረሱም።

# ደጋጎቹ !


ተፈራ ሃ/ማርያም


ግርማ ነጋሽ


ጥበበ ተ/ማርያም


ጥላሁን ገ/ሥላሴ


አልማዝ ምህረቴ


እፀገነት ስዩም


አንዳርጋቸው ሙሉጌታ



መስፍን በቀለ


አርቲስት ታምሩ ወ/አብ


ጌታቸው በቀለ


ሰይፈ አበበ


ወርቅነህ ወ/ሃና


አለማየሁ ፈረጃ


ሰለሞን ሃድጎ


ነስጥ አስፋው

# 5. ዘመን ተሻጋሪ ነዋሪዎቻችን ሲታወሱ

## 5.1 አባባ ሳላ ደቻሳ

አድዋ ዘምተው በውጊያ የወደቁ ጀግኖቻችንን አንስተው በክብር ቀብረዋል።ቁስለኞችን አክመዋል አስታመዋል። ከአድዋ መልስ በዐፄ ምንሊክ ታላቁ ቤተመንግሥት ባለሟል ሆነው አገልግለዋል። በዐፄ ሀይለሥላሴ ዘመን በሰገሌ በተደረገ የእርስ በርስ ጦርነት ዘምተው በአድዋ የከወኑትን ደግመዋል።

እኝህ ባለታሪክ አቶ ሳላ ደቻሣ (አባባ ሳላ) ይባላሉ። ሀፄ ምንሊክ በ1902 የምንሊክ ሆስፒታልን መርቀው ሲከፍቱ አብረዋቸው በቦታው ተገኝተው የምንሊክን ንግግር አዳምጠዋል። ለምረቃው በአል እለት ዙፋናቸው የተዘረጋው ዛሬ በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ላቦራቶሪ ፊት ለፊት በቆመው ሀውልታቸው አጠገብ ነበር። "በሽተኛ ይፈወስብሽ፣ አዛውንቶች ይጦሩብሽ፣ ልጆች ይደጉብሽ" ብለው ሀፄ ምንሊክ ሲመርቁ አባባ ሣላ አድምጠዋል።ታሪኩንም ዛሬ በህይወት ላሉት አዛውንት አስይዘዋል። ይህ ብቻ አይደለም ንጉሡ የቤተ መንግስት አሽከርነት ይብቃህ በዚህ ሆስፒታል ደመወዝ ተቆርጦልህ ከነጮቹ ጋር ሆነህ ተማርና ወገንህን እርዳ በማለት የመኖሪያ ቦታ ሰጥተው አስናበቷቸው። አባባ ሣላም የምንሊክን ቃል አክብረው ከፈረንጆቹ ተጠጉ።



አባባ ሳላ ኧኚህ ነበሩ

ፈረንጆቹ የሚሰሩትን ቀሰሙ ያለምንም ዘመናዊ ዕውቀትና ትምህርት የመድሀኒት ቀማሚ (chemist) ሆኑ ስማቸው ገነነ። ህመምተኛው ከሳላህ እጅ መድሀኒት ካልተቀበለ የሚፈወስ አልመሰልህ አለው።

ይህ ብቻ አይደለም ለበዐላት ቀናት የመጠጥ አረቄ በእጃቸው ቀምመው ታዳሚውን ያስፈነጥዙ ነበር። የአቶ ሳላና የምንሊክ ሆስፒታል ታሪክ የማይነጣጠሉ ሆነዋል። ዐፄ ምንሊክ በሰጡዋቸው ቦታ ጎጆ ቤት ሰርተው ሲኖሩ ዐፄ ሀይለሥላሴ ምንሊክ ሆስፒታልን በአንድ ወቅት ሲጎበኙ ሳላ የት አለ አሉ? ጥሩት ብለው አስቀርበው ቤትህን አሳየኝ አሉዋቸው። ጎጆውን አሳዩዋቸው ከሆስፒታሉ ግንባታ የተረፈ ቆርቆሮ እንዲሰጣቸው አዘው የሰሩት ቆርቆሮ ቤት ዛሬም አለ።

አቶ ሣላህ ደቻሣ በሥራና በጡረታ ለረጅም ዐመታት ኑረው በ1968 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ አይረሴ ኗሪያችን ነበሩ። ነፍሳቸውን ከነአብርሃምና ከሣራ ጎን ያኑርልን።

## 5.2 ጋሼ አረሩ ገድሌ

ጋሼ አረሩ ገድሌ

ሌላው ከማይዘነጉት ነዋሪዎች መካከል ከጥቂቶቹ አንዱ ሃረሩ ገድሌ ነው : :
ጋሼ ሃረሩ ለልጆች የላቀ ፍቅር ነበረው ከህጻናት ጋር ውሎ ቢያድር ደስታው ነው። ልጆችም ሰብሰብ ብለው ይፈልጉታል። የአለበትን ለማግኘት በየአቅጣቻው ተከፋፍለው ይቃኛሉ። አንድ ቡድን ሲያገኘው በፉጨትና በጩኸት ተጠራርተው ተሯሩጠው ይከቡታል። እርሱ ዘለግ ባለው ቁመናው ከመሀላቸው ሆኖ ጃቡሌ፣ ጃቡሌ ሲል ልጆቹ ተቀብለው ጃቡሌ አረሩ ገሌ ይሉታል። ከልቡ ይጨፍራል። የከበቡት ልጆችም የምራቸውን ይጨፍራሉ። ጋሽ ሃረሩ በማህበራዊ ህይወቱ በሰፈሩ ኗሪዎች፣ በህፃናትና በአዛውንቱ ታዋቂና ተወዳጅ ነበረ። በህይወቱ ከሳቅ፣ ከቀልድና ጨዋታ በስተቀር ከፍቶት አያውቅም። ጽኑ የቤተክርስቲያን አገልጋይም ነበር። የጋሼ አረሩ መልካም ፈቃድ ካልታከለበት ካህንም ቢሆን ሰንበቴ ቤት አይገባም። የሰንበቴ ታዳሚዎች ከበሉ ከጠጡ በኋላ በቀልድ ያዝናናቸዋል። ከአጠገባቸው እንዲርቅ አይፈልጉም። እርሱ ግን ምጥን ያለ ፈገግታ ከአላባሳቸው በኋላ ወደ የሚያፈቅሩትና የሚያፈቅራቸው ልጆቹ ዘንድ መሄድን ይመርጣል። ይከቡታል። ጃቡሌ አረሩ ገሌ እያሉ አብረው ይጨፍራሉ፤ ይደንሳሉ በአካባቢው የሚንቀሳቀሱትን ኗሪዎች ቀልብ ይስባሉ የጋሼ አረሩ ትዝታ ዛሬም መቼም አይረሳም ፣ ነፍሱን ከአብርሃምና ከሳራ ጐን ያኑርልን።

## 5.3 ቴምባና ደጴና፡ ከአይረሴዎቻችን መካከል

ቴምባና ደጴና ከማይዘነጉት ጥቂቶቹ ናቸው ቴምባ ቀበና የመጣው ከትውልድ ሥፍራው ጋምጎፋ ነው። ሁለቱም እንደሌሎቹ የሀገራቸው ተወላጆች ሸማ የሚሠሩ አልነበሩም። ኧረ እንደውም ምንም የሚሠሩት አልነበረም። ሁለቱም በየዕለቱ በማናቸውም ሰዓት ጥግብ ብለው በኮሪያ ሰፈር ጎዳና ላይ ወዲያ ወዲህ እያሉ መንገደኛውን ፈገግ የሚያሰኙ ሰላማዊ ጠጪዎች ነበሩ።

ቴምባ በወር ሁለት ቀን ሥራ እንደነበረው አንድ አብሮ አደጋችን ነግሮኛል። ቅዳሜ ከምሽቱ ከ10-12 ሰዓት እና እሁድ ከጠዋቱ 2 ሠአት እስከ 6 ሰአት ሳቅ የሚያስጭረው የቅዳሜው ሥራ ነው። ለዕድርተኞች የክፍያ ቀንና ሰአትን በጥሩንባ የሚያውጅባት ሥራ ጥሩንባውን በረጅሙ ይነፋና የአከሌ እድርተኛ የሆናችሁ ነገ ክፍያ ስለ አለ በ2 ሰዓት ወይም በ3 ሰዓት ወይም በአራት ሰዓት ወይም በአምስት ሰዓት . . መጥታችሁ እንድትከፍሉ ይላል። ይህን በዞረበት ሁሉ ይደጋግማል። የዕድሩ አመራር በየጊዜው ከ2 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ብለህ ተናገር ይሉታል። ቴምባ እሺ ይላል አንድም ጊዜ ግን አላሻሻለም፡ቴምባ ከስጋ ብልት ሁሉ ነብሮ ይወዳል ተመስገን የሥጋ ቤቱ ባለቤት ይወደዋል።አንድ ሙዳ ነብሮ ይሰጠዋል። ፊቱን ወደ ተመስገን አዞሮ ሥጋውን በጥርሱ ያዝ ያደርግና ቢላዋን ከከንፈሩ ሥር ሽቅብ ወደ አፍንጫው ሰንዝሮ ሥጋ ይቆርጣል። ሰከንድ በማይሞላ ጊዜ አንድ ሙዳ ጭጭ ያደርጋል። ተመስገን በአበላሉ ይደሰታል።

ቴምባ ወደ ጠጅ ቤት ይሄዳል። ጋባዥ መቼም አያጣም ጥግብ ሲል ከጠጅ ቤት ወጥቶ ባገኘው ቦታ ጋደም ይላል። እልም ያለ እንቅልፍ ይወስደዋል።

ደጴና ሸማ ሥራ ሞክሯል። ከመንደሩ ሴቶች ልቃቂትና ቀብድ እየተቀበለ ባለበት ቀን ማስረከብ የሚሳነው ሸማኔ ነበር። ቀብዱንም ሆነ ሴቶቹ የፈተሉትን ልቃቂት እርሱ ቦታ አስይዟቸዋል። ሸጦ ጠጥቶበታል። ጭቅጭቅ ሲበዛበት የሸመና ቦታውን እርግፍ አድርጎ ተወ። የሚገርመው ገንዘብ ከየት እንደሚያገኝ ባይታወቅም በየቀኑ ድብን ብሎ በሬሣ በር መንገድ ተጀንኖ ሲመላለስ ይታያል። ደጴና ቢጠጣም ትእግስተኛ ነው። መሰደብና መዘለፍን አጥብቆ ይጠላል።

ይህን የሚያደርግ በእጁ ከገባ ቢያንስ የወር ሀመሙን ያገኛል። ታዲያ ጠጥቶ አመሻሽቶ በፈለገበት ሰዓት ለአዳር የሚሄደው ቀበሌ 06 ጽ/ቤት ነው። ማንም ከልካይ የለውም። በር ተከፍቶለት አዳራሽ ገብቶ ጭድ ላይ ተኝቶ ያድራል። አንዳንድ አብዮት ጥበቃዎች ማደሪያ ከከለከሉት በማግሥቱ ከሚጠጡበት ቤት ገብቶ ይደቁሳቸዋል። በመሆኑም ከልካይ አልነበረውም። እርሱም እንደቴምባ ሰፈሩን ለቅቆ የገባበት አይታወቅም። ቴምባና ደጴና በዘመናቸው የኮሪያ ሰፈርን ተዝናንተውበታል፡ ኗሪውንም የሚያዝናኑ ነበሩ። በህይወት ካሉ ዕድሜና ጤና እንመኝላቸዋለን። ከሌሉም ነፍሳቸውን ከአብርሃምና ከሣራ ጎን ፈጣሪ እንዲያሳርፍልን እንፀልያለን ።

## 6. የቀበና ልጆችና የጋሼ ታምሩ ትዝታዎች



ጋሼ ታምሩ ዮሴፍ

ከሪያ ዘምተው ቀበና መኖሪያቸውን ከመሠረቱት የክብር ዘበኛ ጦር አባላት አንዱ ናቸው። ግዳጃቸውን ተወጥተው እንደተመለሱ መደበኛ ሥራቸው ታላቁ ቤተ መንግሥት ነበር። ጠንቃቃና ኩሩ ሾፌር ነበሩ፡ በጽዱ አለባበሳቸው ከአንገታቸው ከሚያስሩዋቸው ምርጥ ምርጥ ከራቫቶችና ከእጃቸው በማይለያቸው በትረ መኮንን ተብሎ ከሚታወቅ ውብ ዱላ ጋር በቀበና ኗሪዎች ይታወቃሉ። ለአዛውንት፣ ለጎልማሳው፣ ለሴቱና ለወንድ ሞቅ ያለ ሠላምታ በመስጠትም የሚታወቁ ናቸው።በዕድር አመራር ብቃትና ችሎታቸው እስከዛሬ የሚወዳደራቸው አልተገኘም ብል ማጋነን አይሆንብኝም

**የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ** ዕድርን ከ 30 ዓመታት በላይ መርተዋል። 09 ቀበሌ የሚገኘውን ዕድር የመሠረቱትና በጤና እክል እስከለቀቁበት ድረስ የመሩ ጠንካራ ሰው ናቸው።ዛሬም ሆነ ለወደፊቱ የዚህ ዕድር ስም በአባላቱ ተጠርቶ አያውቅም። እየተጠራ ያለው የጋሼ ታምሩ እድር እየተባለ ነው። ምን ይሀ ብቻ ባልደራስ ተብሎ የሚታወቀውን የቤተመንግስት ጡረተኞች ባህላዊ ምግብ ቤት ከመሠረቱት አንዱ ነበሩ። ለረጅም አመታት በሊ/መንበርነት አስተዳድረውታል።

**. . . ያ የሚንደባለለው ጓደኛችን አሁንም ጥያቄ አነሳ "ጋሼ ታምሩ ሸቅብ መንደባለል እኮ አይቻልም አለ። እሳቸው መቼ ዘዴ ያጡና በደረትህ እየተሳብክ ውጣ አሉት። እኛ በዱብ ዱብ እርሱ በመንደባለልና በመሳብ ላብ በላብ . . .**

ጋሼ ታምሩ ከቀበና ልጆች በተለይ በሾላው ዙሪያና በጄኔራል ደበበ ጫካ ውስጥ በምትገኝ ትንሽ ቦታ ላይ እንጫወት የነበርን ልጆች የማይረሳ ትዝታዎች አሉን። ትምህርት ቤት ሲዘጋ ቢይ፣ ቀስትና ሞር የምንጫወትው በእነዚህ ሜዳዎች ነበር። ጋሼ ታምሩ በወቅቱ እኛ በመጥፎ ስነ-ምግባር ውስጥ እንዳንገባ ጥብቅ ክትትል ያደርጋሉ። ከላይ የጠቀስኳቸውን ጨዋታዎች ሲጫወት የተገኘ ልጅ በጋሽ ታምሩ የሚደርስበት ቅጣት በጊዜው እጅግ አስፈሪ ነበር። ቢይ ተበልቶ ከጨዋታው ውጭ የሆነ ልጅ ብይ ማፈስ የሚችለው የጋሽ ታምሩ መምጣትን ድንገት ጮክ ብሎ ተናግሮ ሮጦ ሲደበቅ ነው። ተጫዋቾች ስማቸው በመጠራቱ ብቻ እግራቸው ወደ መራው እግሬ አውጪኝ ሲሮጡ የተደበቀው ዘዴኛ የተደረደሩትን ቢዮች አፍሶ ይወስዳል።

ለጋሽ ታምሩ መሰል ጨዋታዎች ዱርየነት ነበሩ። ስለሆነም ማንኛችንም ለጨዋታ ስንወጣ በጥንቃቄ የጋሽ ታምሩ በመንገድ ላይ መኖር ያለመኖር በመቃኘት ነው።

መቼም የማልረሳው ገጠመኝ አለ። አንድ እናት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ልጃቸውን ለማስተዛዘን አስራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ከመኝታ ቤቱ ተቀምጠናል። በቁጥር አምስት ነበርን። ጋሼ ታምሩ መጡ ሁላችንም ደንግጠን ቆምን። ዱላቸውን እወዛወዙ አይናቸውንም አጉረጠረጡብን ብርክ ያዘን ምን አባታችሁ ታደርጋላችሁ ብለው አባረቁብን። መልስ የለም ዝም ብለን ዓይን ዓይናቸውን ተመለከትን። ቆይ ግድየለም ስመለስ ላግኛሽ ብለው ለቅሶ ቤት ገቡ። እኛም ተንስተን ጄኔራል ደበበ ጫካ ውስጥ ተደበቅን። መውጣታቸውን ስንከታተል ቆይተን ሲወጡ ተመልሰን ገባን ካርታ ጨዋታ ጀምረን የተሟሟቀ ሁኔታ ውስጥ እያለን ከየት መጡ ሳይባል ከች ብለው አንተ ዱሬዬ ወሮበላ ሁሉ መውጫም የላችሁ ተነሱ ከነካርታችሁ አሉን። ተነሣን በቅደም ተከተል በሰልፍ ውጡ አሉን። በሚያስፈራራ ድምፃቸው አወጡና ሾላው ሥር ወስደው ቁጭ በሉ ተባልን እንዳሉን አደረግን። ከሱ ሳትነሱ ዱብዱብ እያላችሁ ወደታች ቀጥሉ አሉን ዱብዱብ ጀመርን' ይከተሉናል። ወደ ኋላ የቀረውን በዱላቸው መቀመጫውን ዠለጥ ያደርጋሉ። ታዲያ ከመሃላችን አንዱ ትንሽ ዱብዱብ እንዳለ ተፈነገለ ዱላ ቀመሰና ቀጥል ሲሉን ጋሼ ታምሩ እግሬ በሽተኛ መሆኑን እያውቁምና ነው እንደ አላቸው። ነው አሉና በል ተንከባለል አሉት።

እሽ ብሎ ቁልቁል ወደ እሳቸው ቤት መግቢያ ተንደባለለ እኛ በእሱ መንደባለል እንስቃለን። በመሳቃችን አንዳንድ ዱላ ከወደኋላችን ይመርቁልናል። ታች መገንጠያው እንደምንም ስንደርስ ወደ ሾላው ሽቅብ ቀጥሉ ተባልን።

ያ የሚንደባለለው ጓደኛችን አሁንም ጥያቄ አነሳ "ጋሼ ታምሩ ሽቅብ መንደባለል እኮ አይቻልም አለ። እሳቸው መቼ ዘዴ ያጡና በደረትህ እየተሳብክ ውጣ አሉት። እኛ በዱብ ዱብ እርሱ በመንደባለልና በመሳብ ላብ በላብ ውልቅልቅ ብለን ሾላው ደረስን።የሚገርመው ነገር የእሳቸው ቅጣት ሳይሆን አመሻሽተው የሚመጡ አባቶች ምን ጥፋት እንዳጠፉን እንኳ ሳይጠይቁ ጋሽ ታምሩ ለእነዚህ ወረበሎች ጥሩ መድሀኒት ነህ እኮ ዋጋቸውን ስጥልን ከማለት አልፈው ይሄማ ዋና ጎረምማ ነው እያሉ አጠገባቸው ያገኙትን ልጅ በኩርኩም ያቀምሳሉ። ቅጣቱ ከተፈፀመ በኋላ ዛሬ መሽቷል ነገ በሰባት ሰዓት ቤት ድረስ መጥታችሁ እንድትፈርሙ አንድሽ ብትቀሪ አታምልጭኝም በሚል ማስጠንቀቂያ ተለቀቅን በማግስቱ በትዕዛዙ መሠረት ለፊርማ ተሰባስበን ሾላው አጠገብ ስንጠብቃቸው መጡ። ከመኪናቸው እንደወረዱ አፍጥጠው ወደ እኛ መጡና ቢይ ለመጫወት ነው የተሰባሰባችሁት አይደል አሉና የትናንት ምሽት ቅጣት ደገሙና አንድ ወደታች አንድ ወደላይ በዱብ ዱብ ላብበላብ አድርገው በማስጠንቀቂያ ለቀቁን ደግነቱ የዛን ቀን የተንከባለለውና በተሳበው ቅጣት በመታመሙ አለመምጣቱ በጀው። እሳቸውም ማን እንደቀረም አልጠየቁም።

አድገን ሥራ ከያዝን በኋላ ይህን አንስተን ስንጫወት እሳቸው ብቻቸውን ናቸው እኛ ሮጠን ማምለጥ ስንችል ለምን ዝም ብለን ያን ፍዳ አየን ብለን እንጠይቃለን። መልሱን ራሳችን እንመልሰዋለን በዚያን ዘመን የሚቀጣህ፣ የሚገስጽህ ሁሉ አባትህ፣ ሱቅ የምትልክህ ሁሉ እናትህ ነበሩና ከአባትና ከእናት አይመለጥም። ጋሽ ታምሩ የሴፍ የዚያ የእኛ የልጅነት ዘመን የጋራ አባታችን ነበሩና። ማምለጥም ከቶም አናስበውም ነበር።ጋሽ ታምሩ የሴፍ ዛሬ በህይወት ባይኖሩም እኛ በህይወት እስካለን ድረስ ከልባችን አይጠፉም። እግዚአብሔር ነፍሳቸውን በመንግስተ ሠማያት ያኑርልን አሜን።

# 7. ሐኪም ሜዳ እና ትዝታዎቼ

እኔ ለቀበና ብሎም ለኮሪያ ሰፈር አንጋፋ መሆኔን ለሚያውቅ ሰው ምነው ጃል! ምንነካህ! የጨዋታ ሜዳውን አጠበብከው፣ ይልቅ ሰፋ አድርገህ ስለ ቀበና እና ዙሪያ ገባው ብታጫውተን ሊል ይችላል። እኔም ይሄ ጠፍቶኝ ሳይሆን በልጅነት ዘመኔ በውል ከማውቃትና እሹሩሩ ብላ ካሳደገችኝ የእድሜ ዘመን ትዝታዬ ከሆነችውና እንቀልባዬን ከሰቀልኩባት ሃኪም ሜዳ ተነስቼ ወደተቀረው ብንደረድር ያም ርብኛል በማለት ነው።

እኔ ስገምተው በአካባቢው በመጀመሪያ የተወለደ የመጀመሪያው ብቸኛ ሕጻን ሳልሆን አልቀርም። ምክንያቱም አባቶች እንደሚነግሩኝ "ስፈጭም አገዜ ስቆላም አገዜ ጀርባዬ ተላጠ ውረድ ከጀርባዬ" እየተባለ እሹሩሩ የተዜመለት ብቸኛው ህጻን እኔ ነኝ ስለዚህ ስለሐኪም ሜዳና አካባቢው የዘመን ትውስታዬን ባወጋችሁ ያምርብኛል እንጂ የሚጎፈንናችሁ አይመስለኝም ለማለት ነው።

እድሜህ ስንት ቢሆን ነው አትበሉኝ እድሜ ድሮ በሞኙ ጊዜ እንደ ብር እየተመነዘረ እንደ ሳንቲም እየተዘረዘረ የሚረጭበት ዘመን አልፏል። አንድ የእድሜ ጓደኛዬ እንደሚለው "እድሜ ውድ መረጃ ነው"።

ወደ ዋናው ጉዳይ ከመግባታችን በፊት በቅድሚያ የሃኪም ሜዳን የተፈጥሮ አቀማመጥ በምናባችን ለአንድ አፍታ በወፍ በረር መቃኘቱ ተገቢ ነው።

ይህ ሜዳ ሃኪም ሜዳ የሚል መጠሪያ የተሰጠው የምኒልክ ሆስፒታልን የምሥራቅ በር ወይንም የሆስፒታሉን የጀርባ አጥር ተንተርሶ የተቀመጠ መሆኑ ይመስለኛል። እንደሚባለው በዛን ዘመን ሜዳው ላይ የሆስፒታሉ ታማሚዎች የሚጠቀሙበት እንሶላ ታጥቦ የሚሰጣበት ስፍራ ነበር።ከሜዳው በስተ ግርጌ በቅርብ ርቀት የሚያዋስነው በጀርመን ድልድይ ስር አቋርጦ የሚያልፈው የቀበና ወንዝ ነው። አቤት ያ ወንዝ በበጋው ሲንፎለፎል በክረምት ደግሞ ሲገማሸር ላየው ጉድ ነበር። ዛሬማ ታሪክ ሆኖ ቀርቷል። "ተረት ተረት አንድ ቀበና የሚባል ወንዝ ነበር" ይላሉ የዛሬዎቹ የሐኪም ሜዳ ሕጻናት።

ሃኪም ሜዳ ዛሬ ስሙ ነው እንጂ ግራ ቀኙ የኮንቴነር ቤት ተሰርቶበት የእግር መንገድ ያህል ስፋት ያለው ቦታ ብቻ ቀርቷል። ስም አይቀበርም ሆነና ዛሬም አካባቢው ሃኪም ሜዳ ይባላል - ወግ ነው! ታዲያ ሐኪም ሜዳ በነዚህ ሁለት ዓውዶች መካከል ተሸጉጣ ትገኝ የነበረች ዙሪያውን በጫካ የተከበበች ውብ አረንጓዴ ሜዳ ነበረች።

የሃኪም ሜዳ አካባቢ ነዋሪ በአብዛኛው በሥራ ምክንያት ከገጠር አካባቢ በመጡ ሰዎች የተቆረቆረ በመሆኑና የመሬት አቀማመጡም ሆነ የእጽዋቱና የእንስሳቱ መስተጋብር የገጠርነት መልክ ስለነበረው የህብረተሰቡ ወግና ሥርዓት ገጠር ቀመስ ነበር ማለት ይቻላል። ፈንጠር ፈንጠር ብለው ከተሰሩት የሳር ጎጆ ቤቶች በጣሪያቸው በኩል ሾልኮ የሚዋጣው የሚትጎለጎል የኩበት ጭስ ለአካባቢው ገጠር ቀመስነት አንድ ምልክት ነበር። በአካባቢው እርሻ ባይኖርም በዙሪያው ካሉ ደኖች እንጨት ይሰበርበት አጋምና ቀጋ ይለቀምበት እንደነበር እናውቃለን/ ታውቃላችሁ።

ውሃ የሚቀዳው ወንዝ ተወርዶ ከምንጭ ነበር እናቶች እንዳች በሚያክል እንስራ ውሃ ተሸክመው ጫን ጫን እየተነፈሱ ሽቅብ ወደ መንደራቸው ሲወጡ አውቃለሁ። ልብስ ለማጠብ ከተፈለገ የሚታጠበው ጨርቅ ተሰብስቦ በካሊም /በወቅቱ እንደ እንሶላ ያገለግል ነበር/ ተጀቡኖ ይታሰርና እናቶች በጀርባቸው አዝለው ቀበና ወርደው ከሃይሌ ዱቤ /ልብስ አጣቢ የነበረ/ ጋር የማጠቢያ ቦታ በመሻማት እድል ከቀናቸው አጥበው እዚያው የቀበና ወንዝ ከፈጠረው አለት ድንጋይ ልበሱን አስጥተውና አድርቀው አመሻሽ ላይ ከቤት ይገባሉ። ሃይሌ ዱቤም ሆነ የኮሪያ ሰፈር ነዋሪዎች ልብሳቸውን የሚያጥቡት ከዱቤ ባህር እናት የሁለት ወንዞች መገናኛ ሥፍራ ላይ ነው። ምክንያቱም እዚህ ቦታ ላይ ድንጋዩ ለአጠባ የተመቻቸና ተፈጥሮ ሠራሽ ገንዳ ስለሆነ ነው። /ስለሃይሌ ዱቤና የዱቤ ባህር ወደ በኋላ እናወጋለን/



የሀኪም ሜዳ ቀደምት ነዋሪዎች አባቶችና እናቶች ከመጀመሪያዎቹ በኩር ሕፃናት ልጆቻቸው ጋር (ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ መሆናቸው ይታወቅ)
ከግራ ወደ ቀኝ የታዬ አባት (አለቃ አየለ እንየው ወታደር) ሕፃን ታዬ፣ የታዬ እናት (ወ/ሮ አዳም ተመስገን)፣ የደመቀ እናት (ወ/ሮ ፅጌ ከበበው) የደመቀ አባት (፺ አለቃ ጀምበሬ ደለለኝ) የደመቀ እናት ከልጃቸው ደመቀ ጀምበሬ ጋር



የሀኪም ሜዳ ቀደምት ነዋሪዎች መካከል
እማማ ማንጠግቦሽ ከጉረቤቶቻቸው ጋር

ቀበና በዚያን ዘመን እንዲህ የዋዛ አልነበረም። ከዳር ቆመው ትክ ብለው ካዩት እራስ አዙሮ አቅልን ያስታል። በክረምት በተለይ የተበጠበጠ ድልህ መስሎ ቁልቁል ሲንደረደር ለአካባቢው ነዋሪ ያሸብራል። መስከረም ጠብቶ በጋው ተግ ሲል ደግሞ ውሃው ይጠራና ኩል ይመስላል በዚህ ጊዜ ዱቤ ባህር ሳይቀር ቂም ቋጥሮ ኑ ዋኙኝ ዋኙኝ ይላል።

በዚህ በበጋው ወራት ታዲያ ሁሉም የሠፈሩ ኩታራ ከወላጅ እየተሸሸገ ወደ ቀበና ይወርዳል ትዝ ከሚለኝ ነገር ጎረምሳ ለመሆን ከነበረን ጉጉት የተነሳ ጡታችንን በውሃ እናት /ወንዝ ውስጥ የምትገኝ ብርማ ቀለም ያላት ትንሽ ነፍሳት ነች/ ለማስነከስ ነፍሳቷን ከውሃ ውስጥ አግኝቶ ለመያዝ የምናደርገውን ትግል ሳስበው አይ ልጅነት ጅልነት ያሰኛል።

አንድ ጊዜ እንዲሁ ጢም ለማውጣት በሚል አገጫችንን እና ምናምናችንን በአህያ ፋንድያ ስንፈትግ ውለን እኔ በወንዙ ውሃ ሳልታጠብ ማታ ከቤት እገባለሁ የዛን ጊዜ የነበረው ፋንድያ ትክክለኛው ፋንድያ /ኦርጋኒክ ፋንድያ/ ስለነበረ ሽታው ኃይለኛ ነበር። ታዲያ አባቴ ማታ ሲገባ ይሸተውና ቆጣ ብሎ እዚህ ቤት የምን አህያ ነው ያስገባችሁት ይላል እናቴም ተከትላ አንተ አህያ ወጥተህ ታጠብ ትለኛለች። እኔም ተደናግጬ እየወጣሁ እያለሁ አባትና እናቴ ሲሳሳቁ ሰማሁ ለምን እንደሳቁ ግን የገባኝ ዘግይቶ ነው ለመጎርመስ ያለኝ ጉጉት ገርሟቸው ነው።

አሁን ወደ መነሻ ጉዳያችን ልመልሳችሁና በዚህ ባልኳችሁ ዘመን ሃኪም ሜዳና አካባቢው እንደ ዛሬው ብዙ ነዋሪ ያልሰፈረባት ጥቂት የሳር ጎጆ ቤቶች ፈንጠር ፈንጠር ያሉም ቢሆን የቆርቆሮ ቤቶች የተሠሩባትና ሰንሰልና ባህር ዛፍ የሚበዛባት አካባቢ ነበረች። ነዋሪው ቀበና ወንዝን ከግርጌው አድርጎ የሰፈረበት ምክንያት ለመጠጥና ለመሳሰለው አገልግሎት የሚውል ውሃ በቅርብ ለማግኘት በማሰብ ነው ይባላል። በተጨማሪም ሰፋሪው በክፊል ወታደርና በምኒልክ ሆስፒታል ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ስለሚበዙበት ለሥራ ቦታቸው ቀረቤታ ፍለጋ ነው የሚሉም አሉ። ነዋሪው መነሻው ገጠር በመሆኑ የነዋሪው ወግና ባህል አካባቢው ገጠር ገጠር እንዲሸት አድርጎታል።

**በጊዜው** የወተት ላሞች የሚያረቡና የሚያልቡ ብዙ የአካባቢው ሰዎች እንደነበሩ ይታወቃል። የከብቶቹ እረኛም ጋሼ አበበ ይባሉ ነበር እኛም ብንሆን ቀደም ብለን የገጠር ልጆች አንሁን እንጂ አስተዳደጋችን የከተማ ልጆች ነን ለማለት አያስደፍርም። ልብሳችን ቁምጣ ሱሪ እንደነበር ሁሉም ያውቃል። አባቶችም በአዘቦቱ ቀን ኩታ አጣፍተው የሚለብሱ እናቶችም ጉንፍ ያለው እስከ እግር ጥፍራቸው የሚረዝም ሐበሻ ቀሚስ ይለብሱ እንደነበር እንደህልም እንደህልም

እስቲ አሁን ደግሞ ወደ ሃኪም ሜዳ የህጻንነት እይታዬ ልመልሳችሁ ማደግ አይቀርም ከእዝል ወርጄ እግር ሳወጣ የሃኪም ሜዳን ዙሪያ ገባውን፣ በሜዳው የሚግጡትን ከብቶች፣ በሰማይ የሚበሩትንና በዙሪያው ባሉ ትልልቅ ዛፎች ላይ ከአንዱ ወደ ሌላው ዛፍ እየበረሩ የሚዘምሩትን አእዋፍ መለየት ጀመርኩና የእንስሳቱን አፈጣጠር ቅርጽና ቁመና በማየት መደነቅ ጀመርኩ።

በዚህ ቅጽበት አይኔም ተከፈተ፣ ጆሮዬም ክፉና ደጉን መለየት ጀመረ እግሬም ባገኝበት መርገጡን ተወና ቦታ ይመርጥ ጀመር ወዲያው በዙሪያዬ ብዙ ህጻናት ከበውኝ አገኘሁ። እነዚህ ህጻናት የሃኪም ሜዳ አብሮ አደጎቼ ወንድሞቼና እህቶቼ ሆነው ለሚቀጥሉት ረጅም ዓመታት በክፉና በደጉም አብረውኝ የሚዘልቁ ናቸው።

በዚህ ዘመን ሃኪም ሜዳ ዙሪያውን እስከ ቀበና ድረስ በደን የተሸፈነ ነበር ታዲያ ለቡሄና ለመስቀል ዱላ የምንቆርጥበት ለችቦ የሚሆን ከሴ ከአስታ እያማረጥን የምንለቅመው ከዚሁ ነበር። ለሜዳው ግርማ ሞገስ የሚሰጡት በሜዳው ዙሪያ ግዙፍ የሆኑ የባህር ዛፍና የፅድ ዛፎች ነበሩ ብለን ብለን ሲደክመን በጥላቸው ስር የምናርፍባቸው መጠለያ ዎቻችን ነበሩ። የአካባቢው ነፋሻነት ወቅቱን ጠብቆ የተመጣጠነ ስለነበር በጤንነት እንድናድግ አግዞናል።

ሃኪም ሜዳ በወቅቱ ሳሩ የሚታጨድና ለከብቶች መኖ ለማድረግ በሜዳው መሐል ሳሩ ይከመር ነበር ታዲያ በዚህ ጊዜ ለእኔና ለጓደኞቼ ሰርግና ምላሽ ነበር። ከክምሩ ጫፍ ላይ ለመውጣት የነበረው ፉክክር እንደገና ደግሞ ከክምሩ ላይ ቁልቁል እየተንከባለሉ መውረድ ታዲያ በዚህ ጊዜ አንዱ ሲወድቅ ሌላው ሲነሳ የተቀረው ሲሮጥ መልሶ ደግሞ ከመሬት ሲፈርጥ ለቅሶም ሳቅም እየተደበላለቀ ለህጻንነት አእምሮአችን ልዩ ስሜት የሚሰጥ ነበር።

**በዛን ዘመን** ሃኪም ሜዳን የሚያክል ሜዳ ያለ አይመስለኝም ነበር። በኋላ በአንድ የጥምቀት በዓል በእናቴ እየተጎተትኩ ጃል ሜዳ ስደርስ ጉድ አልኩኝ! ለእኔ ትልቁ ሜዳ ሐኪም ሜዳ ይመስለኝ ነበር። ለካስ ጃል ሜዳ በሃኪም ሜዳ ላይ ምላሱን ሲያወጣበት ኖሯል። ከዛን ጊዜ ወዲህ እኔ ሃኪም ሜዳን ናቅ ናቅ ማድረግ ሃኪም ሜዳም እኔን ገፋ ገፋ ወደ ማድረግ ሆነና እንደ ቀድሞው ላንሆን ለዘላለም ተለያየን ልቤ ወደ ጃል ሜዳና አካባቢው ሽፈተ ጉርምስናም ተከተለና ወትሮ የሚጣፍጠኝ እየመረረኝ፤ ይመረኝ የነበረው ደግሞ እየጣፈጠኝ ግራ ተጋባሁ ለካስ ይህ የህይወት ሚስጥር ኖሯል።

አሁን ወቅቱን ጠብቆ ሌላ ዘመን መጣ ሁሉም ለአቅመ አዳም ደረሰ ከአንድ የዕድሜ ምዕራፍ ወደ ሌላው ከፍተኛ የዕድሜ ምዕራፍ ተሸጋገርን። በቃ የልጅነት ጊዜ አበቃ "ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ" አሁን ሁላችንም እንደ እንስሳ የዛሬውን ብቻ ማሰብ ትተን ስለ ነገ ማሰብ ጀመርን። ልጅነት ትዝታ መሆን ሲጀምር እኛም ጨመትን የማናውቀውን አወቅን የማያውቀንም አወቀን እድሜያችን አሾሩጦ ሌላ አዲስ ህይወት ውስጥ ከቶን ሳናስበው ራሳችንን በሌላ ቦታ አገኘነው እቤት የጊዜው መሮጥ! ጥድፊያው ለምን እንደሆነ ይገባችኋል እኔ እቀድም እኔ እቀድም እኮ ነው።

በዚህ ዘመንም ቢሆን እኔና እኒያ ቀደምት የልጅነት ጓደኞቼ አልተለያየንም። ይልቁንም የልጅነት ፍቅራችን ጎመራና ሌላ አንድ የሚያደርገን የሚያሰባስበን ነገር ማሰብ ጀመርን። በዚህ መካከል ነው የሃኪም ሜዳ አብሮ አደጎች ሰብስብ እርሾ ሆኖ ቃኘው በኮሪያ የተባለ የአብሮ አደጎች ማህበር በ1960ዎቹ መጀመሪያ የተወለደው።

ቃኘው በኮሪያ የሚለው መጠሪያ ስም የተመረጠው የብዙዎቹ አባቶቻችንን የኮሪያ የጦር ሜዳ ውሎ ለመዘከር ታስቦ ከመሆኑም ባለፈ የአካባቢው መጠሪያ ጭምር በመሆኑ ነበር።

ቃኘው የሚለው መጠሪያ በኮሪያ ልሳነ ምድር አባቶቻችን ከፈፀሙት ታሪክ ጋር የሚያያዝ ነው። እ.ኤ.አ. ከግንቦት 1951 እስከ ህዳር 1954 ድረስ ኢትዮጵያ 6037 የንጉሠ ነገሥቱን የክብር ዘበኛ ምርጥ ወታደሮች በኮሪያ አዝምታለች። በተባበሩት መንግስታት ወታደራዊ ዕዝ ስር በተካሄደው በዚህ ወታደራዊ ዘመቻ፡-


| | |
|---|---|
| 253-------- | ውጊያዎች ተደርገዋል |
| 120------- | ተሰውተዋል |
| 536-------- | ቆስለዋል |
| ምርኮኛ ------ | የለም |

እጅግ የሚገርመው ነገር ኢትዮጵያውያን በሚዋጉበትም ሆነ የመከላከል ግዳጅ ላይ አንድ ቀን እንኳን ተሸንፈው አለማወቃቸው ነው። /ምንጭ- the story of the Ethiopian Fighter in Korea by Kumon Skordiles)

በመሆኑም ይህ ማህበር በተለይ በክብር ዘበኛ ጦር መምሪያ በኩል ከፍተኛ የአገልግሎት እገዛ ይደረግለት ነበር። ይህ ማህበር የራሱን ጽ/ቤት ከፍቶ ከአባላት በሚሰበሰብ መዋጮ እራሱን ያስተዳድር የነበረ ጠንካራ ማህበር ነበር።

ማህበሩ በተለይ በ1960ዎቹ አጋማሽ በርካታ የአካባቢውን ወንዶችና ሴቶች በማህበር አባልነት አካቶ ሁለገብ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ በአካባቢው ሕብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ ማህበር ነበር።በወቅቱ ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች መካከል የድራማ፣ የሙዚቃ፣ የሽርሽር፣ የስፖርትና የስነ-ጽሁፍ ዝግጅቶች ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ነበሩ።

በተለይም የድራማና የሙዚቃ ክፍሉ በአዲስ አበባ ውስጥ እንደ ማዘጋጃ ቤት፣ ወወክማ፣ ኮከበ ጽባህ ባሉ አዳራሾች ጭምር ዝግጅቱን ያቀርብ ነበር። በወቅቱ ይቀርቡ ከነበሩት ተወዳጅ ዘፈኖች መካከል ዘነበች ከማልኪ፣ ያባቦሌ፣ አሾኮኮ፣ ከእንግሊዝኛው ደግሞ አቫናቲ ዋን አቫንቲቱ የሚጠቀሱ ናቸው።



## የሐኪም ሜዳ ቀደምት ጉብሎች

ከግራ ወደቀኝ የቆሙት ጥላሁን ገ/ሥላሴ፣ ታዬ እየለ፣ ፍቃዱ ሳህለድንግል፣ ዮናስ አሰፋ፣ በጋዬ ታደሰ፣ ደመቀ ጀንበሬ
ከግራ ወደቀኝ የተቀመጡት እንድአርጋቸው ሙሉጌታ፣ ሐብታሙ እየለ፣ አገኘ ተሾመ ፣ ጥበበ ተክለማርያም (1960 ዓ.ም ቀበና ፎቶ ቤት)



**ጃፓኗን ወድጄ !!**
**ከመሀል ያሉት ወታደር እየለ እንየው**
**(በኮርያ ዘመቻ ወቅት ጃፓን ሀገር )**

በተለይ ለማስታወስ ያክል በወቅቱ አቀንቃኞች የነበሩት

- ወገኔ ፀጋዬ የጀምስ ብራውንን ዘፈን ሃርት ብሬከርን አይ አም ቤገር እያለ ተጫውቷል።
- ፀጋዬ ቶሎሣ (ኦቦ) የአማርኛ የተለያዩ ዘፈኖችን
- ተክስተ ዮሃንስ (በክራር የትግርኛ ዘፈን)
- ዘወድነሽ ሃይሌ (በኋላም በአገር ፍቅር በድምፃዊነት ስትሰራ የነበረች) ቀለሜዋ የተሰኘውን ዘ ፈን
- ግርማ ማሞ ሚኒ ሚኒስከርት የተባለውን ዘፈን
- ሳሙኤል ደሬሣ እሾ ቦኩ የኦሮምኛ ጨዋታ
- አይናለም ተስፋዬ (ቡጡቃ በኋላ ታዋቂ አርቲስት ለመሆን የበቃችው በሴት ዘፋኝነት
- አስራት አለማየሁና ባንኬ ሃይሌ በጃዝ መቺነት

እንዲሁም ከአዲስ አበባ ውጭ እንደ ሶደሬ ባሉ መዝናኛ ቦታዎች ጭምር ማህበ አባላቱን ያዝናና ነበር። አልፎ ተርፎ እስከሆለታ ገነት በመሄድ በወቅቱ ለነበ የሆለታ ገነት ጦር አካዳሚ እጩ ተመራቂዎች ሳይቀር ዝግጅቱን አቅርቧል።


**በወቅቱ** ይቀርቡ ከነበሩ ድራማዎች መካከል "ባባቱ ዳፋ ልጁ ተደፋ" በሰው ድግስ ሳንቀላፋ ያስረገዘኝ ጠፋ፣ "እንዲሁም የአንድ ቀን መዘዝ ያለዘጠኝ ወር አይመዘዝ" የሚሉት ዛሬ ትዝታን ከሚቀሰቅሱት አስተማሪ ድራማዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

እነዚህ ሁሉ ዝግጅቶች በብዙ ገጠመኞችና ትውስታዎች የተሞሉ ናቸው። ታዲያ አልፎ አልፎ ዛሬም አብረውኝ ከዘለቁት አብሮ አደግ ጓደኞቼ ጋር ስንገናኝ ጨዋታችን በሙሉ እነዚህን ገጠመኞች ማንሳትና መጣል ነው።

በአንድ ወቅት ባባቱ ዳፋ ልጁ ተደፋ የሚለው ተውኔት በሙዚቃ ታጅቦ በኮከበ ጽባህ ት/ቤት ዋና አዳራሽ ውስጥ ሊታይ ዝግጅቱ ተጠናቋል።በጊዜው ብርቅ የነበረው የድምጽ ማጉሊያ በአዳራሹ ግራና ቀኝ ተሰቅሎ አካባቢውን ቀውጢ አድርጎታል። እድሜ ለክብር ዘበኛ ሙዚቀኛ መምሪያ። ህዝቡ የዝግጅቱን ሽብ እረብ አይቶ በግፊያ ወደ አዳራሹ ገባ። አዳራሹ ጢም ብሎ ግቢ ነፍስ ውጪ ነፍስ ሆነ። በረጅሙ ቁልቁል የተዘረጋው የአዳራሹ ቀይ መጋረጃ ግራና ቀኝ ለሁለት ተከፈለ ዝግጅቱም ተጀመረ።

ታዳሚው አዳራሹን በጭብጨባ አናጋው። አስተዋዋቂው በኩራት ተጀንና የዝግጅቱን ፕሮግራም ሊያስተዋውቅ ብቅ አለ ተመልካቹ በድጋሚ በከፍተኛ ጭብጨባ ተቀብለው አስተዋዋቂው በደስታ ተሞላ ፈገግ እንደማለት አለና በእንግ ሊዝኛ ዌልካም በጣሊያንኛ ቱቲማንቱቲ /የፋገራ ጣልያንኛ መሆኑ ነው/ ቀጠለ በፈረንሳይኛ አሁንም ቀጠለ። ሲጨርስ የፕሮግራሙን ቅደም ተከተል ገለፀ በመጀመሪያ አለ አስተዋዋቂው ትዊስት ወደ ግራ ትዊስት ወደ ቀኝ እራቴን ስበላ ፍቅርሽ አነቀኝ የሚለውን ዘፈን እክሌ በውዝዋዜ ታጅቦ ያቀርብ ላችኋል ከሙዚቃው በመቀጠል ባባቱ ዳፋ ልጁ ተደፋ የሚባለውን ድራማ እናቀርብላችኋለን ብሎ ወደ መልበሻ ክፍሉ ገባ።

ሴቶቻችን /ዳንሰኞቹ/ ከፊት ለፊት ወደ ታች ሙሉውን በሚያብለጨልጭ ወርቅማ ቁልፍ ወደታች የተዘጋውን ቀይ አንድ ዓይነት ቀሚሳቸውን ለብሰው በሰልፍ ዓይነት አገባብ ወደ አዳራሹ ብቅ አሉ። ዳንሰኞቹ ሁሉም የአካባቢው ኩታራዎች መሆኑን ተመልካቹ ሲያውቅ በድንጋጤ ዝም አለ አላጨበጨበም' የሙዚቃ መሳሪያም የለም። እንዲሁ ጭብጨባና ሆታ ብቻ ነው። ዝግጅቱ ተመልካቹንም ሆነ አዳራሹን የሚመጥን ባለመሆኑ እድምተኛው ፊት ነሳ። ቢሆንም ዘፈን ተብዬው አለቀና አስተዋዋቂው



ጉረምሶቹ . . .

ከግራ ወደቀኝ የቆሙት ጥበበ ተ/ማርያም፣ ታዬ አየለ፣
ግዛው ደበበ ከግራ ወደቀኝ የተቀመጡት ብርሃኑ ተከሌ፣
እንድአርጋቸው ሙሉጌታ፣ (1965 ዓ.ም በሕብረት ፍሬ ት/ቤት)

ተመልሶ ወደ መድረክ መጣ። የድምጽ ማጉሊያውን ጨብጦ በዝግጅቱ እንደተደሰታችሁ በማመን አሁን ደግሞ ባባቱ ዳፋ ልጁ ተደፋ የሚለውን ተውኔት የመጀመሪያው ምዕራፍ ይቀርባል አለ። ተመልካቹ ግን አላጨበጨበም' ደብሮታል። ድራማው ቀረበ የባስ አታምጣ ድራማው ይባስ ብሎ የልጆች የእቃ እቃ ጨዋታ ይሆንበታል። በዚህ ጊዜ ተመልካቹ እጅግ ተበሳጨ ድራማውም እንደምንም ተወለጋግዶ አለቀ። አስተዋዋቂው ፊቱን ኮስኩሶ ማስታወሻውን እያገላበጠ በድጋሚ ብቅ አለ። የተመልካቹ ስሜት እንደተበላሸ ገብቶታል አሁን ደግሞ አሻንቲዋን- አሻንቲ ቱ የተባለ የጣልያንኛ ዘፈን እናቀርባለን ብሎ ብዙም ንንግሩን ሳያበዛ ፈጠን ብሎ ተመለሰ። ተመልካቹ ጆሮውን እየኮረኮረውም ቢሆንም ዘፈኑን ጨረሰ ድራማው ግን መቀጠል አልቻለም። ድራማ የሚባል ነገር አታንሱብኝ አለ ተመልካቹ የድራማ ነገር ሲነሳ ኡኡ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል ተመልካቹ። አስተዋዋቂው ተቸገረ በዚህ ምክንያት ሁለተኛውና ሶስተኛው ክፍል ሊቀጥል አልቻለም።

አስተዋዋቂው በተመልካቹ ግፊት ምክንያት በፕሮግራሙ መሠረት ድራማውን ማስቀጠል አልቻለም። ይህ ሲሆን ዋናው የድራማው ተዋናይ




**ቴክሶቹ!**

ከግራ ወደ ቀኝ ጥበበ ተ/ማርያም፡ ተከስተ ዮሐንስ፡ ከበደ አጉናፍር፡ ታዬ አየለ፡
ሰዩም፡ ገብረወልድ፡ ግርማ ነጋሽ፡ እንዳርጋቸው ሙሉጌታ (ሆለታ ገነት ከተማ 1960ዎቹ መጨረሻ

እኔ ተዘነጋሁ በሚል ከመልበሻ ክፍል ውስጥ ሆኖ ይዘላል ይፈርጣል አሁንም ይህ ተዋናይ ወይንም የድራማው መሪ አስተዋዋቂውን በፕሮግራሙ መሠረት መድረክ እንዲሰጠው በድጋሚ ይማጸናል። ተመልካቹ ግን አምርሯል። የድራማ ነገር ሲነሳ አዳራሹ ይበጠበጣል፣ አንፈልግም፣ አንፈልግም ይላል። ለሁለተኛ ለሶስተኛና አራተኛ ጊዜ ድራማው ተዘለለ። አሁን ይህ ተዋናይ እራሱን መቆጣጠር አልቻለም ነቀለ። በኋላ በቀጥታ ከመልበሻ ክፍሉ ውስጥ እየተንደረደረ ይወጣና ከመድረክ ላይ ቆሞ ያስተዋውቅ የነበረውን አስተዋዋቂ አንድ ጊዜ በቡጢ አፍንጫውን ይለውና ለድራማው መልክ ይስጡልኛል ብሎ የያዛቸውን ደም መሰል ቀለምና በርካታ የብር ኖቶችን በመድረኩ ላይ ወርውሮ እጁን እያወናጨፈና እያጉተመተመ ተመልሶ ወደመልበሻ ክፍሉ ይገባል። አሁን ተመልካቹ ያልጠበቀውን አሪፍ ድራማ በማየቱ አዳራሹ በሳቅና በሁካታ ይሞላል። "እይ የልጅ ነገር አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ" ተመልካቹም ለምስኪኑ ተዋናይ ያዝንና ድራማው እንዲቀጥል ተደርጎ እንደምንም ይጠናቀቃል። በወቅቱ የነበረው አስተዋዋቂ የዛሬው ዶ/ር ብርሃኑ ተከሌ ሲሆን ተዋናዩ ደግሞ ታዬ አየለ ነበረ።

ወደ ዋናው ጉዳያችን ልመልሳችሁና የስድሳ ስድስቱ አብዮት ሲፈነዳ የአካባቢው ወጣት ፍቅርና ግንኙነት የመጨረሻ ከፍተኛ ጫፍ የደረሰበት ነበር ማለት ይቻላል። በአብዮቱ መነሻ ወቅት በርካታ የማህበሩ አባላት በእድገት በሕብረት ዘመቻ ተሳታፊ በመሆን ከአዲስ አበባ ውጭ በየጎጡ ተበተኑ። ይህ ለቃኘው በኮሪያ ማህበር ብሎም ለአካባቢው ወጣቶች ቀጣይ ሕልውና የመጨረሻው መጀመሪያ ነበር ማለት ይቻላል። በወቅቱ በበጎ አይን ስላልታየ የቃኘው በኮርያ ጽ/ቤት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዳግም ላይከፈት ተዘጋ ቀሪ አባላቱም በየጓዳ ጎድጓዳው ተሸሸጉ።



ዘማቾቹ!!

**እድገት በሕብረት 1967 ዓ.ም**

ከቀኝ ወደ ግራ ግርማ ነጋሽ፣ ሰዩም ገብረወልድ፣ ታዬ አየለ፣ ታደሰ ...፣ እንድአርጋቸው ሙሉጌታ፣ መላኩ አለነ፣ አማረ አጉናፍር፣ የተቀመጠው ግርማ ዘውዴ

**በመካከል ያለውን** ታሪክ ሆድ ይፍጀው። የማያልፍ የለም ያ ክፉ ዘመን አለፈ "አለፈ ከተባለ" ውሎ አድሮ ከነበርንበት ስንባንን የነበረው እንዳልነበር ሆኖ ቀድሞ በሕልማችንም ሆነ በውናችን ባልገመትነው ሥፍራ እራሳችንን አገኘነው። ግማሹ ሞቷል፣ የተቀረው ተሰዷል ከፊሉ ፊዞ ደንዝዞ ካለበት ቦታ ሳይነቃነቅ ያንን የልጅነት ዘመኑን ትዝታ እያመነዠገ ቁጭ ብሏል።

ታዲያ ዛሬ ያንን የልጅነት ወርቅ ጊዜ በትዝታ መነጽር ወደኋላ ብዙ ዘመን ተጉዘን ስናየው ባናገኘውም ይናፍቀናል በትዝታውም እንጽናናለን። የወጋችን መነሻ ሐኪም ሜዳ ነበረችና ጨዋታዬን ከመጨረሴ በፊት ጥቂት ስለ ሐኪም ሜዳ ግጥም ብጤ ላቅርብና ወጌን ላጠቃልል።

## ግጥም ዘ ሐኪም ሜዳ

ዛሬ የብረት ጉማጅ መጣያ፣
ትላንት የኔ፣ የኒያ ጓደኞቼ መዋያ
ተደስተን የምንውልብሽ
ከሰፊው መስክ ለምለም ሜዳሽ

ለእንቁጣጣሽ እንግጫ
ለመስቀል አደይ አበባው ቢጫ፣
የሚነቀልብሽ ነበርሽ ሃኪም ሜዳዬ
ሃኪም ሜዳዬ አዬ
የተላበስሽው ልምላሜ
እውነት ያንቺ ነበር አለሜ
ነው ወይስ እኖርብሽ ነበር በልሜ?

የፀዳልሽ አረንጓዴነት ድምቀት
የሜዳሽ ልምላሜ ውበት
እጅግ ድንቅ ነበር በእውነት
አይ ውበት . . . አይ ውበት . . .

በወግ በስርአት ያሳደግሽኝ፣
ልማድ ባህሌን ያስተማርሽኝ
የናት የአባቴን ያወረስሽኝ፣
እማማዬ ነሽ ሃኪም ሜዳዬ፣
ሃኪም ሜዳዬ
አዬ
ዛሬ ብታይኝ አታውቂኝም
አርጅቻለሁ አትለይኝም
ግና ከከርሰ ማህፀንሽ ነኝና አትርሺኝም።

ጉልበቴ ደክሞ ከንዴ ዝሏል
አይኔም ታክቶት አጮልጭሏል።
ግን እማማዬ ሃኪም ሜዳ
ደስ ይበልሽ ተከቻለሁ ላንቺው እዳ።

ለነገሩማ አንቺስ የት አለሽ
የብረት ጉማጅ ተጭኖሽ
ላነሳልሽ ብዬ ደከመኝ
የዋዛም አልከበደኝ

እማማዬ የልጆችሽን ሃዘን ሰማሽ
እስኪ ላርዳሽ ካልሰማሽ
እንደከበደኝ አይቀር ጭራሽ
ጥበብ ኩታሽ ተገፈፈ
ግርማ ሞገስሽ ረገፈ
ጥላሽ ከላይሽ ታጠፈ

እንግዲህ እርም አውጪ ሃኪም ሜዳዬ
እኔ ብቻዬን ምን ተዳዬ
ምን ነካቸው ግን አትበይኝ
የምስጥሽ መልስም የለኝ
ብቻ ጠፉ ተያይዘው
ላይመለሱ ቀሩ በዛው
አይ ሰው . . . አይ ሰው . . .

መግለጫ
በግጥሙ ውስጥ የብረት ጉማጅ ማለቴ ሜዳው በነበረበት ቦታ ላይ የኮንቴነር ቤት የተሰራበት መሆኑን

# 8 . ኃይሌ ድቤ እና ድቤ ባህር


ኃይሌ ዱቤ ከ1940ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ እስከ 1960ዎቹ መጀመሪያ የነበረ ዘመን ተሻጋሪ የቀበና ልብስ አጣቢ የነበረ ሰው ነው።

የኃይሌ ዱቤ ትክክለኛ መጠሪያ ስሙ ኃይሌ ዶቢ ነው።ዶቢ ትክክለኛ የአባቱ ስም ነው ግን ከዱቤ ባህር ሥር ተለይቶ ስለማያውቅ ኃይሌ ዱቤ ተባለ ይላል ታምሩ ወ/አብ መንግሥቴ በጻፈው ክብ እሩጫ በሚለው መጽሐፉ ውስጥ፡-

ታምሩ ወ/አብ እንደሚለው ኃይሌ ዱቤ የሚመጣው ከአራት ኪሎ አካባቢ ነው።እያሰለሰ ቀኑ ሞቅ ሲል ዘወትር ወደ አራት ሰዓት ገደማ አንዳች የሚያክል በአንሶላ ተወጥሮ የተጠቀለለ ጨርቅ በአናቱ ተሸክሞ ከአራት ኪሎ ተነስቶ በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በኩል አሳብሮ በሬሳ መውጫ በኩል የነበረችውን ቀጭን መንገድ ተከትሎ ሾላውን በግራ በኩል ይተውና ቁልቁል ወርዶ በእማማ ብሬ /ቢኬሬ/ ቤት በር ያልፍና ወደ ቀበና ይሻገራል።

የጉዞ መስመሩና ሰሀቱ ሳይስተጓጎል ይኸው ነው ታዲያ ወታደሩም የወታደር ልብሱን በአሚዶ አድርቶ ተኩሶ የተኮሰው መስመር እንዳይሰበር እራሱን ወጥሮ ቀስ እያለ ወደ ላይ ከብርዘበኛ መምሪያ ለቆጠራ ሲሄድ ኃይሌ ዱቤ ወደ ታች ሲወርድ ዘወትር ይገናኛሉ። ኃይሌ እንዴት አደርክ ይላል ጀነን ብሎ ወታደሩ ኃይሌም እግዜር ይመስገን ይላል። ወታደሩ መልሶ ሚስቶቻችንን አደራ ብሎ ቀልዶ ያልፋል።እንደሚባለው ኃይሌ ዱቤ አጠባውን ከጨረሰ በኋላ መንደሩ ውስጥ ካሉ ሴቶች ጋር ነው የሚውለው ገሚሱ ቡና ያፈላለታል ገሚሱ እንጀራ በሚጥሚጣ ይሰጠዋል የሚጠጣም ካለ ጠላ ከጠፋ ቅራሬውን ያቀርቡለታል። በዛን ዘመን ማንም ይሁን ማን አንድ ሰው ሌላው ሰው ቤት ገብቶ እንዲህ በዋዛ አይወጣም። የተገኘውን እንዲቀምስ በሞቴ፣ አፈር ስሆን እንክት ስል፣ እየተባለ ይለመናል። እሱም አርባ አራቱን ታቦት እየጠራ ጠላትሽን / ጠላትክን አልገባም እቸኩላለሁ ይላል። እሺ ብሎ ከገባ ያው የማይቀረው ቡና ይፈላለታል። ቤት ያፈራውም ይቀርብለታል። አይ ደግ ጊዜ ታዲያ ኃይሌ ወደ ወንዝ ሲወርድ ዘወትር ከእጆቹ የማይጠፉ ሶስት ነገሮች አሉ።

አንደኛው ሽክሙን ደገፍ አድርጎ የሚይዝበት ቀጭን ከዘራ ሲሆን ሌላው በጨርቅ የተጠቀለለ ጥቁር የጭቃ ሳሙና ነው። የተቀረው ሳሙናውን የሚያፈላበት የማይሌክስ የዱቄት ወተት ቆርቆሮ ነው። ኃይሌ ዱቤ የልብስ አጠባ ያቀነጨረው መዳፈ ሰፊ፣ የእግሩ ባት የፈረጠመ አጭር ጠይም አንድ አይና ሰው ነው። ኃይሌ ዱቤ በዚህ ዓይነት ሂደት ዓመታትን አሳልፏል። ታዲያ በሃዘንም ሆነ በደስታ ከስራሩ ነዋሪ አይለይም። ኃይሌ ዱቤ ከቀበና ወንዝ እንደ ደረሰ የተሸከመውን ጨርቅ ከማጠቢያው የድንጋይ ገንዳ ይነከርና በሁለት እግሩ ገብቶ ጨርቁን እየረገጠ ማንጎራጎር ይጀምራል። ሌላ ዘፈን አይቀላቅልም ሁልዜ ዜማውም ግጥሙም አንድ ነበር። "እረ ሙኖ ሙኖ" ብቻ ታዲያ ጨርቁን በግራ እግሩ ገልበጥ ገልበጥ ያደርግና አንዴ በቀኝ እግሩ ጠብሰቅ አድርጎ ይረግጠዋል። ይህንን በደጋገመው ቁጥር ውስጡን' ውስጡን' ውስጡን' ይላል ታዲያ በአካባቢው ያሉ አጣቢዎች ሴቱም ወንዱም በዚህ የተለመደ ዘይቤው እየተዝናኑ እነሱም አጠባቸውን ያለድካም ያከናውናሉ።




**አፍቃሪዎቹ !! (1960 ዎቹ)**

**ቀበና ድቤ ባህር አካባቢ (ውይይት በፍቅር ደብዳቤ ዙሪያ)**
**ከግራ ወደ ቀኝ ጥበበ ተ/ማርያም፣ ብርሃኑ ተክሌ (ዶ/ር)**

አሁን ደግሞ ጥቂት ስለዱቤ ባህር ላውጋዎት ዱቤ ባህር የሚታወቀው በአስፈሪ ግርማ ሞገሱ ነው። አጋንንት ከነ ቤተሰቡ እረከቦቱን ዘርግቶ እግሩን አንሰራፍቶ የነገሰባት ጥልቅ ባህር ነው።

ይህ ባህር የሚገኘው ከአቦና ከፈረንሳይ አካባቢ የሚመጡት ሁለት ወንዞች በሚገናኙበት ሥፍራ ላይ ነው። ታዲያ ዱቤን እንደዋዛ የቀረበው ካለ እንደ ማግኔት በሚስብ ኃይሉ ወደ ውስጥ ጎትቶ ያስገባና አስምጦ ያስቀራል።ሰይጣኑና ቤተሰቡ ተጠራርተው ደሙን እንደ ዋገምት ምጥጥ አድርገው ከጨረሱ በኋላ ሲሻቸው በጉብስማም ይሁን በቀይ ዶሮ ደም ተለማምነው ወደ ዳር አስከሬኑን ይተፉታል።ካልተመቻቸው ደግሞ ጉሮሮውን አንቀው ይዘው አንለቅም ይላሉ። በዚህን ጊዜ ለእሳት አደጋ ይደወላል በዚያን ጊዜ ስልክ የሚደወለው አንድ ነበዝ ይመረጥ ና በሩጫ ተሄዶ ከቃዲ ደጅ ወይንም አባ አብደላ ሱቅ ነው። እሳት አደጋ በዋዛ አይመጣም።በዚህ ጊዜ ጋሼ ልበለውና ሰው ዱቤ ባህር ገባ ከተባለና ሲጮህ ከሰማ ከእሳት አደጋው መኪና እሱ ይቀድማል። ጋሼ የእስፖርት ቁምጣውን ያጠልቅና ከላይ ደግሞ ለጦር ኃይሎች የስፖርት ቀን ከዘመናት በፊት ለገመድ ጉተታ ሲወዳደር የተሰጠውን የወየበች ባለማንጠልጠልያ ግራጫ ከናቴራውን ይለብስና ረዥም ቀጭን አጠናውን ይዞ ሰውን ግራ ቀኝ እየገፈተረ ዘሎ ከባሕሩ ይገባል።

> ኃይሌ ዱቤ የልብስ አጠባ ያቀነጨረው መዳፈ ሰፊ፣ የእግሩ ባት የፈረጠመ አጭር ጠይም አንድ አይና ሰው ነው።



**ቡጢኞቹ !! 1960ዎቹ**

**ቀበና ድቤ ባህር አካባቢ**

ከግራ ወደ ቀኝ ጥበበ ተ/ማርያም፣ አታክልት ብርሃኑ፣ ግርማ ዘውዴ፣ ታዬ አየለ፡ የተቀመጠው አንዳርጋቸው ሙሉጌታ

"ዱቤ ቢደፈርስ ቢመስል እንቶቶ ጋሬጣው ጎጃሜ ገባው ባጭር ታጥቆ" የተባለለት ጎበዝ ወታደር ነበር ደመቀ ዶሪ ይባላል። ቤቱ የት ነበር መሰላችሁ ከዱቤ ባሕር ሃምሳ ሜትር ያህል ከፍ ብሎ ወደ ቃዲ ደጅ በሚወሰደው መንገድ በስተ ግራ በኩል ከነበረው ዛኒጋባ ቤት ውስጥ ነበር።

ታዲያ ያሁሉ ሆኖ ሰው ከነ ህይወቱ አይገኝም ነበር። አስከሬኑም ከተገኘ የተረፈ ያህል ነበር።ዱቤን ከጋሼ ቀጥሎ የሚደፍረው ኃይሌ ዱቤ ነው። ከላይ የሚታጠብ ልብስ ውሃ ነጥቆ የሚወስደው ጨርቅ ሂዶ የሚያርፈው ዱቤ ባሕር ውስጥ ነው። ታዲያ በዚህ ጊዜ ለኃይሌ ዱቤ ሠርግና ምላሽ ነው። ኃይሌ ዱቤም በፈረንካ ወይንም በጣሳ ጠላ ይደረደርና ዘሎ ከባሕሩ ጥልቅ ይልና ያለአንዳች ችግር ጨርቁን ይዞ ይወጣል።ሃይሌ ዱቤ ጥሩ ጨርቅ አጣቢ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ዋናተኛም ነበር።ያም ሆኖ ግን ኃይሌ ዱቤ ለዱቤ ባሕር ብርቱ ሚስጥረኛ እንደሆነ ይታማ ነበር።

ይህ ባህር ዛሬ ከሞቱ አሟሟቱ ብሶ ለምልክት እንኳን በሚያስቸግር ሁኔታ ጠፍቷል። እንደነገርኳችሁ ይህ ባህር ሁለቱ ወንዞች ከላይ ተወርውረው የሚገናኙበት በመሆኑ፣ የሚፈጠረው የውሃ ሽክርክሪት ድንጋዩን ቦርቡሮ ከባሕሩ የታችኛው ክፍል ጥግ ዋሻ ቢጤ የባጀ መሆኑ የታወቀው ባሕሩ ደርቆ እርቃኑን ሲቀር ነው።ሰውም ሆነ የሰመጠ ማንኛውም ነገር ይገኝ የነበረው ከዚህ ዋሻ ውስጥ ነበር እንጂ በዛን ዘመን እንደሚባለው ከጋኔኑ የእልፍኝ አዳራሽ ውስጥ አልነበረም። ይህን ሚስጢር ግን ኃይሌ ዱቤ ሳያውቅ አይቀርም ብዬ እጠራጠራለሁ። ዛሬ ኃይሌ ዱቤም፣ ዱቤ ባሕርም የሉም ትዝታቸው ግን ዛሬም ከእኛ ጋር ነው።

> "ዱቤ ባህር ዛሬ ከሞቱ አሟሟቱ ብሶ ለምልክት እንኳን በሚያስቸግር ሁኔታ ጠፍቷል።"



**ዘናጮቹ!**

ከግራ ወደ ቀኝ አታክልት ብርሃኑ፡ ግርማ ዘውዴ፡ ብርሃኑ ተክሌ፡ ታዬ አየለ፡ ተክስተ ዮሐንስ፡ ጥበበ ተ/ማርያም፡ አንዳርጋቸው ሙሉጌታ (ቀበና ድልድይ 1960ዎቹ መጨረሻ)

# 9. የቀበና ስፖርት ትውስታዎች

> ". . . የቀበና እግር ኳስ ሲነሳ ትልቅ ዝናና ታሪክ የነበረው የቀበና ናዳ እግር ኳስ ቡድን የሚዘነጋ አይሆንም ብዙዎቻችን የቀበና ቲፎዞዎች ነበርን . . ."

ስፖርት ስንል ሩጫዎች ዝላዮች፣ ውርወራዎች፣ ውሀ ዋና፣ እግር ኳስ፣ ክብደት ማንሳት እና ሌሎች ያልተጠቀሱ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ያጠቃልለ ነው።

ቀበና ኮርያ ሠፈር በእያንዳንዱ ዲሲፒሊን ስም ያላቸው ወጣቶችን አፍርቷል በ1940ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ላይ ለአንጋፋው ለቅዱስ ጊዮርጊስ የእግር ኳስ ተጫዋቾች የነበሩት ነፍሳቸውን ይማርና ጋሽ ለገሰ ወልደሰንበት እና ጋሽ ተካልኝ ታየ የቀበና ፍሬዎች ነበሩ የእነሱን ፈለግ የተከተሉ በርካታ ወጣቶችም ነበሩ ዛሬም አሉ ኑሮዎን በአሜሪካ ያደረገው ጌታቸው በላይነህ (ዶር) የቅዱስ ጊዮርጊስ በ'B' በ'C' ቡድን ተጫዋች ነበረ። ዘውዱ ደበበ አባ ወሎም የአንበሳ ቡድን ታዋቂ ተጫዋች ነበር። ነፍሱን ይማረውና መኮንን ተሰማ 13ኛው የአፍሪካ ዋንጫ በሊቢያ ሲካሄድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋች ነበረ የዛሬን አያድርገውና ቤተ-መንግስት የራት ግብዣ ላይ ተገኝቶ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸልሟል። የከራይ ቤቶች የእግር ኳስ ክለብን በአሠልጣኝነት ሠርቷል።



**ቀበና ናዳ**

ታኅሣሥ 13 ቀን 1966 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እስቴዲየም ውስጥ
ከግራ ወደ ቀኝ ምንዳ ተሰማ ነጋ ተክለሃና፣ ታምሩ አምባቸው፣ አለሙ ኮስታ መኮንን ተሰማ፣ እከሌ፣
የተቀመጡት ትርፌ ጉሹ ቃሲም አብዶ ንጋቱ ገ/ማርያም፣ እከሌ፣ ተስፋዬ ታደሰ (ቅልጥም)

ወጣቱ ፋሲል ተካልኝ ታየ የአባቱን ፈለግ ተከትሎ በቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብ ለአመታት ተጫውቷል በአሳየው ብቃትም ለብሔራዊ ቡድን ብዙ ጊዜ በውጭ ሀገርም በሀገር ውስጥም ተጫውቷል በዚህ አላበቃም የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክበብ ዋና አሠልጣኝ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ምክትል አሠልጣኝ በመሆን ለራሱም ለቀበናም የማይፋቅ ታሪክ እያስመዘገበ ነው የስፖርት ክበብ በማቋቋም ረገድም የኮርያ ሠፈር ወጣቶች አልቦዘኑም በ1950 መጨረሻ ዓመት ላይ ኢትዮ ፔይንት በሚል ስያሜ በአንጋፋዎቹ የቀበና




1969 ዓ.ም የቅዱስ ጊዮርጊስ እግርኳስ ቡድን
በቀስቱ የተመለከተው ምንዳ ተሰማ ነው

ወጣቶች ተመስርቶ ነበር ለዚህ ክበብ ምስረታ በገንዘብና በስፖርት ቁሳቁስ ሙሉ ድጋፍ ያደርግ የነበረው የቅዱስ ጊርጊስ ቢራ ፋብሪካ የማስታወቂያ ሰራተኛ የነበረው አቶ ወንድሙ የሚረሳ ሰው አይደለም ይሁንና ዘመኑ በሥርዓትና በመግባባት አብሮ መኖር የማይታወቅበት ጉልበተኛ እንዳሻው የሚያዝበት ነበርና ክለቡ ዳዴ ሳይል በአጭሩ ተቀጨ።

ተተኪው ቃኘው በኮሪያ በኮርያ ተቋቁሞ በስፖርትም በድራማና በሙዚቃ ተሳትፎ አድርጓል በዚህ ወቅት ወታደር ደጀኔ ቱጂ እና ወታደር አለማየሁ ይርዳው ሰለቸኝ ታከተኝ ሳይሉ ማህበሩን በማደራጀት እና በማስተባበር ውለታ ሰርተዋል። አቶ አለማየሁ ይርዳው በሕይወት ባይኖርም በጐ ሥራውን ግን ስናስታውስ እንኖራለን። ወታደር ደጀኔ ቱጂ ጀግና ወታደር ከመሆኑ ባለፈ አሁንም ጀግና ገበሬ ነው። ምስጋናችን ይድረሰው።

የቀበና እግር ኳስ ሲነሳ ትልቅ ዝናና ታሪክ የነበረው የቀበና ናዳ እግር ኳስ ቡድን የሚዘነጋ አይሆንም ብዙዎቻችን የቀበና ቲፎዞዎች ነበርን ነጋ ተክለሃና ግን መስራች ብቻ ሳይሆን ተተኪ የሌለው ምርጥ ተጫዋች ነበር በርካታ ወጣቶች የነጋ ተክለሃና ከዚህ ባለፈም በቡድኑ የመጨረሻ ዘመን አካባቢ ምንዳ ተሰማ የቡድኑ ተጫዋች በመሆን በናዳ ታሪክ ውስጥ ቀበና ኮርያ ሰፈርን እንዲታወስ አድርጓል።

ሌላው የቀበና ስፖርት ትውስታ የመረብ ኳስ ነበር ሁለት ረጃጅም ሽምበቆ በመትከል ገመድም ወይም የጨርቅ ቅንጥፍጣፍ በማሰር መረብ ኳስ መጫወት የተለመደ ነበር ይህን የልጅነት ጊዜ ጨዋታ መሰረት በማድረግ በሙሉ ወጣትነት ዕድሜያቸው የቀበና ልጆች በርካታ ናቸው ለአብነት ያህል ወንድማማቾቹ ረታ ዘውዴ እና ካሳሁን ዘውዴ ዋቆ (አረሩ)

እንዲሁም ታደሰ ካብትይመር የሚጠቀሱ ናቸው ካሳሁን ዘውዴ በመረብ ብቻ ሳይሆን በቅርጫት ኳስ የክለቡ ተጫዋች ነበር የሩጫ ስፖርትን ስናነሳ የረጅም ርቀት ሩጫ አፍቃሪ የነበረው ፈቃዱ ሣህለድንግል (ቢልጮ) ሳናነሳው ባናልፍ አፅሙ ይወቅሰናል እናም የማራቶን ሩጫ ውድድር ከሰፈር ተነስቶ በክብር ዘበኛሆስፒታል ፈረንሳይ ድልድይን ይዞ በቤላ አቋርጦ በጀርመን ኢምባሲ ታልፎ ሽቅብ አድቬንቲስት ሚሲዮን ደርሶ ዳግመኛ በሬሳ በር ሰፈር ሐኪም ሜዳ መድረሱ ነበር ፍቃዱ በፍፁም ሀቀኝነት የሩጫ መስመሩን ተከትሎ ሩጫውን በአሸናፊነት ለመጨረስ ሲታትር ዞር ብሎ ሲመለከት ከኋላው ማንም ባለመኖሩ ልቡ በደስታ እየተሞላ በአሸናፊነት ስሜት ይሮጣል።



የቀበና ናዳ ተጫዋቾች 1965 ዓ.ም



የቀበና ናዳ ተጫዋቾች ከደጋፊዎቻቸው ጋር 1965 ዓ.ም

ምን ያደርጋል ታዲያ ከመነሻው አብረው የተነሱ ጃንሜዳ ሲደርሱ እጥፍ ብለው ጃንሜዳ ይጠብቁና ፍቱ የአድቬንቲስትን ዳገት ጨርሶ ምኒሊክ ብቅ ሲል ከፊቱ በመሮጥ የድሉ ባለቤት የሚሆኑት ሌሎች ነበሩ ፍቱ መሸወድ አይገባውም ቅን ልቦና አለዋ! ሌላ ቀንም እንዲሁ ሁሌ ጥረቱ ለአንደኛነት ቢሆንም በተሸናፊነቱ ግን ተስፋ አይቆርጥም ነበር። ነፍሱን በገነት ያኑርልን።

## 10.የጨዋታ ቦታዎቻችን ትዝታዎች

የቀድሞ የቀበና ልጆች ጨዋታዎች ወቅትን ያገናዘበ ነበር ማለት ይቻላል። በክረምት ትምህርት ቤት ሲዘጋ ዋናው ጨዋታ ብይ ነው። ቀስት ወይም ሞር። ሀኪም ሜዳ፣ ጫካ ሰፈር (አሁን የገበያ ሱቅ የተሰራበት) ኖራ ሜዳና አመቺ ገላጣ ቦታዎችን ያካትታል። በእነዚህ ጨዋታዎች የሚሳተፉት በዕድሜ ተቀራራቢ ቢሆኑም ከመሀከላቸው ጉልቤ ምንጊዜም ይኖራል። ይህ ጉልበተኛ የሆነ ያልሆነ ምክንያት እየደረደረ ያፍራል።

ጨዋታው እንዲደገም ያደርጋል። ከተበላ ደግሞ አስቆጣሪ ይሆናል ባለ እዳውም ደግሞ ለቡሄ ተጨፍሮ ከሚገኝ ሳንቲምና ከእንቁጣጣሽ ከአበባ ከሚያገኘው ሊከፍል ግዳጅ ይጣልበታል የቡሄና የእንቁጣጣሽ እለትና ማግሥት የቆጠረውን ሂሳብ ገቢ ካላደረገ በተገኘበት እየታደነ ካልቾና ኩርኩም ይቀምሳል… ከዚህ ለመዳን እንደምንም ብሎ ገንዘቡን መክፈል ነበር የሚያዋጣው።

ሌላው የበጋ ጨዋታ አግር ኳስና ቦሊቮል በሀኪም ሜዳ ፣ በኖራ ሜዳ፣ ዱቤ ባህር ልብስ ማጠቢያው አጠገብ የምትገኝ ትንሽ ሜዳ ላይ ነው የሚገርመው ጨዋታዎቹ ጊዜ አይወስናቸውም።
ከጠዋት እስከ እኩለ ቀን፣ ከምሣ በኋላ አይን እስኪይዝ መጫወት ነው። የኖራ ሜዳ እንደ ስሙ ሜዳው ኖራ ነው።

እዛ የሚጫወቱ ልጆች መላ ሰውነታቸው ነጭ ነው ሲመሽ ወንዝ ወርደው ታጥበው ወደ ቤት ካልሄዱ የሚጠብቃቸ ቀበቶ ነው። እነርሱም የቀበቶ ግርፋትን ስለሚያውቋ ተንደርድረው ወንዝ ታጥበው ወደ ቤት ይገባሉ። ውሃ ዋና በተለ በጥቅምት ወር ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።የወንዙ ውሃ ኩልል ብሶ የሚጠራበት ጊዜ ስለሆነ ሁሉም ወደ መነጽር መዋኛሥፍ ይሄዳል። ልብሱን አወላልቆ መለመላውን ዘሎ መግባት ነበ ዕፍረት የለም፡ዋኝቶ የጠገበው ከመንፅር ይወጣና ዕርቃኑ ተቀምጦ አሊያም ተጋድሞ ፀሀይን እስኪጠግብ ይሞቅና ተመል ዘሎ ገብቶ ይዋኛል። ከውሃ ዋናም የሚገላግለው ምሽት ነበር።

ሀኪም ሜዳ' ጀነራል ደበበ ጫካ ሜዳ፣ ጫካ ሰፈር ሜዳ፣ ኖ ሜዳ ከልጆች መጫወቻ ቦታዎች ባለፈ አመሻሽ ላይ አባቶች ጋ ወይም ካፖርት ደርበው የሚያወጉት በእነዚህ ሜዳዎች አጠገ ከሚገኝ ጉብታ ቦታዎች ላይ ነበር። ጨለምለም ሲል አባቶ ሰላምታ ተለዋውጠው ወደ የቤታቸው ሲገቡ እናቶች ዕለታ የግብር ውሃ ግዴታቸውን የሚወጡት በእነዚህ ሜዳዎች አጠገ በሚገኙ ጫካዎች ውስጥ ነበር። ዛሬ እነዚህ ስፍራዎች በሙ በአካል የሉም።

# 11. ድሮ እና ዘንድሮ (ከፎቶ ማህደራችን)

## 11.1 - ድሮ




ቃኘው በኮሪያ ስፖርት ማህበር ጽ/ቤት (1965 ዓ.ም)
ከቆሙት ከግራ ወደ ቀኝ ግርማ ዘውዴ፣ ተከስተ ዮሐንስ፣ አታክልት፣ እንድአርጋቸው ሙሉጌታ ከተቀመጡት ጥበበ ተ/ማርያም፣ ታዬ አየለ፣ ብርሃኑ ተክሌ

# የቃኘው በኮሪያ የስፖርት ማህበር አባላት

## በሸርሸር ላይ ሥፍራው ጥንስስ እና አባ ንጉሴ ባህር 1967 ዓ.ም











ከግራ ወደ ቀኝ ታዬ አየለ፣ ላስቴ የተቀመጡት ጥበበ ተክለማርያም፣ አንድአርጋቸው ሙሉጌታ፣ ዮናስ አሰፋ



ከግራ ወደ ቀኝ ታዬ አየለ፣ ጥበበ ተክለማርያም፣ ግርማ ታደሰ

## ከፎቶ ማህደራችን (በዘመን ቅደም ተከተል)


### የቀበና አብሮ አደጎች ማህበር አባላት በተለያዩ ቦታዎች በሽርሽር ላይ 1985-1990 ዓ.ም
















# የቀበና አብሮ አደጎች ማህበር አባላት በተለያዩ ቦታዎች በሽርሽር ላይ 1985-1990 ዓ.ም














ልጆቻችን

# ዘንድሮ (ከፎቶ ማህደራችን)















# ዘንድሮ (ከፎቶ ማህደራችን)










በውጭ የሚገኙ ጥቂት የማህበሩ አባላት (25ኛውን የማህበሩን ምስረታ ሲያከብሩ)


## በውጭ የሚገኙ **ጥቂት** የማህበሩ ሴት አባላት



ከግራ ወደ ቀኝ እጅጋየሁ በፍቃዱ፣ ፀሐይ ተጫኔ፣ ትዝታ ሚደቅሳ



የቀበና አብሮ አደጎች ማህበር የመጀመሪያ የወንድ እና የሴት ማህበራት መሪዎች
ከልጆቻቸው እና ከልጅ ልጆቻቸው የወንድወሰን ተፈራ እና ፀሐይ ተጫኔ



**የመጀመሪያዋ የሴቶች ማህበር ሊቀመንበር በኮረዳነቷ ማነች?**



ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ
St. George Beer
ፕሪሚየም ላገር ቢራ ከ1915 ዓ.ም. ጀምሮ
PREMIUM LAGER BEER
4.5 % Alc. Vol.
Cont. 33cl
የጥራት
የምንጊዜም አጋራችን
ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ
ጊዮርጊስ ቢራ
1915 ጀምሮ
ፕሪሚየም ላገር ቢራ
ከ1915 ዓ.ም. ጀምሮ
PREMIUM
LAGER

# ክርያ ሰፈ.ር ቀበና



## የ25ኛ ዓመት ዝክረ በዓል ልዩ መጽሔት

Design + Print By: